ይጹም ዓይን ይጹም ልሳን ዕዝንኒ ይጹም
እምሰሚዓ ኅሱም በተፋቅሮ፤
(ቅዱስ ያሬድ)

# ስምዐ ጽድቅ



## ማውጫ

፩ አጫጭር ዜናዎች
፫ ርእሰ አንቀጽ
፭ ሪፖርታዥ
፯ ቤተ አብርሃም
፲፪ ቃለ መጠይቅ
፲፮ የሕፃናት ዓምድ
፲፰ ትዝብት
፳ ምሥጢሬን ላካፍላችሁ

## ስምዐ ጽድቅ

የቤተ ክርስቲያኒቱን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን በትምህርትና ሐዋርያዊ አገልግሎት ማስተባበሪያ በጋዜጣ ዝግጅት ክፍል እየተዘጋጀ በወር ሁለት ጊዜ የሚወጣ መንፈሳዊ ጋዜጣ

ጳጉሜን ፭ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ.ም. ተጀመረ

☎ 011-1553555/ 011-1553442
✉ 80078
አዲስ አበባ

የዝግጅት ክፍሉ ኢሜይል
newspaper@eotcmk.org

ምክትል ዋና አዘጋጅ
ወርቅነሽ ቱፋ
ከፍተኛ ሪፖርተር
ካሣሁን ለምለሙ
ሪፖርተር
ረቂቅ መቻል
የገጽ መልክ (Layout) ዲዛይነር
ግደይ ገብሬ
ጸሐፊ
ገነት ታደሰ

# ማኅበረ ቅዱሳን ፲፩ኛውን ጠቅላላ ጉባኤ አካሔደ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን ፲፩ኛውን ጠቅላላ ጉባኤ ኅዳር ፮ እና ፯ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም በማኅበሩ ጽ/ቤት ሕንፃ አካሔደ::

ጠቅላላ ጉባኤው በመንበረ ልዑል ቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ካህናት ጸሎተ ወንጌል እና በብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ቃለ ምዕዳንና ቡራኬ የተከፈተ ሲሆን የዕለቱ መርሐ ግብር በማኅበሩ ሰብሳቢ በአቶ ታምሩ ለጋ የ"እንኳን ደህና መጣችሁ" መልእክት ተጀምሯል::

በጠቅላላ ጉባኤው የመጀመሪያ ቀን ውሎ የ፳፻፲ ዓ.ም እና የ፳፻፲፩ ዓ.ም የውጪ ኦዲት ዘገባን ጨምሮ የማኅበሩ ስልታዊ ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት፣ የኤዲቶሪያል አገልግሎት ሪፖርት የማኅበሩ ኦዲት አገልግሎት ሪፖርት፣ የማኅበሩ ስልታዊ ዕቅድ የአጋማሽ ዘመን ግምገማ እና ቀጣይ አቅጣጫዎች የሚሉ አንኳር ርእሰ ጉዳዮች ቀርበዋል::

በቀጣይ ቀንም ፯ኛው ሀገር አቀፍ ምርጫና የኦርቶዶክሳውያን ተሳትፎ፣ የግቢ ጉባኤያት አገልግሎት በወቅታዊ ጉዳዮች እይታ፤ በኦርቶዶክሳውያን አንድነትና ኅብረት የማኅበረ ቀዱሳን ድርሻ፣ የማእከላት እና የዋናው ማእከል ግኑኝነት ከፋይናንስ አኳያ እንዲሁም የማኅበረ ቅዱሳን ጠቅላላ ጉባኤ ዝግጅት መመሪያ ማሻሻያ ምክረ ሐሳብ የሚሉ አጀንዳዎች ቀርበው በሁሉም ርእሰ ጉዳዮች ላይ በሀገር ውስጥ እና ከሀገር ውጪ ጉባኤውን ሲከታተሉ በነበሩ አባላት ውይይት ተደርጎባቸዋል::

በዚሁ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ብፁዕ አቡነ ፊሊጶስ የደቡብ ኦሞ-ጂንካ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስና የቅድስት ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ የበላይ ኃላፊ፣ ብፁዕ አቡነ እንጦንስ የምዕራብ ሐረርጌ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ፣ ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ የጉራጌ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ እና የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የጠቅላይ ቤተ ክህነት የየመምሪያው ኃላፊዎች፤ ከየማእከላቱ የተወከሉ የማኅበሩ አባላት እና ተጋባዥ እንግዶች ተሳትፈዋል::

ጠቅላላ ጉባኤው እሑድ ኅዳር ፯ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም በነበረው የመጨረሻ መርሐ ግብሩ ማኅበሩን ለቀጣይ ዓመታት የሚመሩትን የሥራ አመራር አባላት በማስመረጥ እንዲሁም አገልግሎት ያጠናቀቁ የሥራ አመራር አባላትን በክብር በመሸኘት ጉባኤውን አጠናቋል::

# ጆርጂያ የሚገኘው የአሜሪካ ኤምባሲ ለጆርጂያ ገዳም ጥገና የሚውል የገንዘብ ድጋፍ አደረገ

**በካሣሁን ለምለሙ**

ጆርጂያ የሚገኘው የአሜሪካ ኤምባሲ ለጥንታዊው የጆርጂያ ጀቫሪ ገዳም ጥገና የሚውል የገንዘብ ድጋፍ ማድረጉን ኦርቶዶክስ ኮግኔት ፔጅ ዘግቧል::

በምሥራቃዊ ጆርጂያ የሚገኘው ይህ ጀቫሪ የተሰኘው ኦርቶዶክሳዊ ገዳም በአሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተገደመ ሲሆን የአሜሪካ ኤምባሲ ለጥገናው ወጭ ያደረገው ገንዘብ ቅርሱ ይዘቱን እንደጠበቀ ለትውልድ ለማስተላለፍ ያለመ ነው ተብሏል::

ይህ ታሪካዊና ጥንታዊ የጆርጂያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ገዳም በዩኒስኮ የዓለም ቅርስ ሆኖ የተመዘገበ ነው:: ስለሆነም የአሜሪካ ኤምባሲ ለገዳሙ ጥገና የሚውል ከአምስት መቶ ሺህ ዶላር በላይ ድጋፍ አድርጓል::

በጆርጂያ የአሜሪካ ኤምባሲ አምባሳደር የሆኑት ኬሊ ዲኛን መንግሥታቸው በጆርጂያ ኦርቶዶክስ ገዳም ላይ ለሚደረገው መሠረታዊ ጥገና የገንዘብ ድጋፍ ማድረጉ በእጅጉ ክብር እንደተሰማቸው ገልጸዋል::

የጆርጂያ ገዳማት ለጆርጂያ ኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች መንፈሳዊ ሕይወት የላቀ ሚና እንዳላቸው የተጠቆመ ሲሆን የረጅም ጊዜና ዘመን ተሻጋሪ ሆነው መገኘታቸው ለመካከለኛው ዘመን የጆርጂያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ህያው ምስክሮች ሆነዋል ተብሏል::



የጆርጂያ ጀቫሪ ገዳም

# ራስን ማደራጀት የቤተ ክርስቲያንን ተቋማዊ አሠራር ማጠናከር ነው

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ እና ሰማያዊ ተልእኮዋን ለመፈጸም በምታደርገው እንቅስቃሴ ውስጥ ከታች ከአጥቢያው ጀምሮ እስከ ቅዱስ ሲኖዶስ ድረስ በሥርዓት የተዋቀረ አደረጃጀት እና መዋቅር ያላት ቤተ ክርስቲያን ናት። ለዚህም ሥርዓተ ቅዳሴውን፣ ሥርዓተ ማኅሌቱን፣ የዐውደ ምሕረት ጉባኤውን፣ የሰንበት ት/ቤቱን አገልግሎት፣ የገዳማዊውን ሥርዓት እንዲሁም የጥምቀት እና የመስቀል በዓላት የመሳሰሉት በተደራጀ እና መዋቅሩን በጠበቀ መልኩ የሚከወኑ አገልግሎቶች መሆናቸውን በምሳሌነት ማንሳት ይቻላል።

ይህን በሥርዓት እና በወግ የተሠራ የቤተ ክርስቲያን አደረጃጀት ከዚህ ቀደም ይከወን ከነበረበት በተለየ የጠበቀ መዋቅራዊ አደረጃጀት መቆም ዘመኑ የሚጠይቀው ዐቢይ ጉዳይ መሆን አለበት። ያለና የነበረው የቤተ ክርስቲያን መዋቅር ከትላንት በተለየ መልኩ እየተጠናከረ ይጓዝ ዘንድ ከትላንት የላቀ ኅብረት፤ ከትላንት የላቀ ሥራ፣ ከትላንት የላቀ አገልግሎት ከቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆች ይጠበቃል።

በ፴፱ ኛው ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ላይ ከቅዱስ ፓትርያርኩ የተላለፈው "የቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆች ራሳቸውን ለመከላከል ይደራጁ "የሚለው አባታዊ መመሪያ ለቤተ ክርስቲያኒቱ የተደራጀ መዋቅር አዲስ ባይሆንም ወቅቱን ያገናዘበ ፤ ቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ እየደረሰ ያለውን አደጋ እና በተከታይ ምእመናንዋ ላይ እያለፈ ያለውን ሰቆቃና መከራ ማዕከል ያደረገ፤ የጠበቀ እና የተቀናጀ አሰላለፍ እንዲኖር የተላለፈ መመሪያ በመሆኑ ሁሉም የቤተ ክርስቲያን ልጅ ትኩረት ሰጥቶ በተግባር ላይ ሊያውለው ይገባል።

ወቅቱ እያንዳንዱ ለብቻው የሚሮጥበት ሳይሆን ያለውን እና የነበረውን መዋቅራዊ አደረጃጀት ጠብቆ በኅብረት የሚጓዝበት፤ ለአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሉዓላዊነት አጥብቆ የሚሠራበት፤ የቤተ ክርስቲያንን የቀደመ ክብር ለመጠበቅ የሚተጋበት መሆን አለበት። ከዘልማዳዊ አሠራር ወጥቶ በሕግ እና በሥርዓት በመሄድ ከዚህ በፊት ለተፈጠረው እና ወደፊት ሊፈጠሩ ለሚችሉ ቤተ ክርስቲያን እና ምእመናን ተኮተር ጥቃቶች የመፍትሔ አቅጣጫ የሚቀመጥበት መሆን ይጠበቅበታል።

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ለመዋቅር ባዕድ ፤ ለአደረጃጀት አዲስ አይደለችም ሲባል ከምእመኑ እስከ ቅዱስ ሲኖዶስ ያለውን የአገልግሎት መርሕ ማለት ነው። ይኽን የተለመደ አሠራር ትኩረት ሰጥቶ መከወን መደበኛ አድርጎ በዕለት ከዕለት ሕይወት መተርጎም፣ከእኔነት ወጥቶ በእኛነት መንፈስ መንቀሳቀስ ፤ የሁሉም ድርሻ አድርጎ መውሰድ አስፈላጊ ነው። ለዚህም በየደረጃው ያሉ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ካህናት፣አብያተ ክርስቲያናት፣ ገዳማት እና አድባራት፣ ማኅበራት፣ የሰንበት ት/ቤት ተማሪዎች እና ሰባክያነ ወንጌል መምህራን ከፍተኛውን ድርሻ ሊጫወቱ ይገባል።

አደረጃጀቱን ለማጠንከር አስቀድሞ የነበረው መዋቅር ክፍተት ምን እንደሆነ መፈተሸ ተገቢ ነው። ምክንያቱም የትላንት ድክመት ነገ ለሚሠራው ሥራ ግብዓት ይሆናልና። ትላንት የታለፈበት መዋቅር የትላንቱን ችግር ለምን እንዳመጣው መፈተሸ ግድ ይላል። ዛሬ ላይ ቆሞ ወደ ኋላ ሄዶ ክፍተቱ የት ጋር እንደተፈጠረ መገምገም ቀዳዳውን ከመድፈን ባሻገር ነገ ለሚፈጠረው ጠንካራ አደረጃጀት መነሻ መሠረት

ሊሆን ይችላልና ሊበረታበት የሚገባ ዐቢይ ጉዳይ ነው።

የነገዋን ቤተ ክርስቲያን ዘላቂ በሆነ ሉዐላዊነት ላይ ለማስቀመጥ እያንዳንዱ ራሱን መከላከል በሚችልበት አቅም ላይ እንዲደርስ መሥራት ያስፈልጋል። በቤተ ክርስቲያን ወግና ባሕል መሠረት አንዱ ሌላውን በጥሞና ሊሠማው ይገባል። ስለ አንዲት ቤተ ክርስቲያን አንዱ ለሌላው ክብር ሊሰጠው ይገባል ፣ስለ ልዕልናዋ ሲባል ከራስ ክበብ ወጥቶ በኅብረት ውስጥ መገኘት ይጠበቃል። ዳርና ዳር ጽንፍ መያዝ እና ለብቻ መቆም ቤተ ክርስቲያንን ዛሬ እየደረሰባት ካለው መከራ ፣ ነገ ሊገጥማት ከሚችለው ፈተና ሊታደጋት አይችልም። ይልቁንም "እርስ በርስዋ የምትለያይ መንግሥት ትጠፋለች፤ . . " ማቴ ፲፪፥፳፭ እንዳለው ወንጌላዊው ከኅብረት የወጣ ግላዊነት ቤተ ክርስቲያንን ለከፋ ነገር ከማጋለጥ የተለየ ፋይዳ የለውም። በመሆኑም እከሌ ከእከሌ ሳይባል በአንድነት መቆም ከማንኛው የቤተ ክርስቲያን ልጅ ይጠበቃል።

ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ልጆችዋ በኅብረት ሆነው ራሳቸውን መከላከል በሚችሉበት መልክ እንዲደራጁ መመሪያ ማስተላለፏ አንዳንዶች እንደሚመስላቸው ከአመፅ ጥሪ ጋር መቀላቀል የለበትም። በቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አገልግሎት ውስጥ የነበረ፣ያለና ወደፊትም የሚኖር መዋቅራዊ አሠራር ነው። በሀገርም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለ በማንኛውም ማኅበረሰብ ውስጥ የሚገኝ እና የሚከወን መሆኑን ጥርጣሬ ውስጥ ያሉ የቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆችም ሆኑ ከውጭ ሆነው በአመፅ መሣሪያነት የሚፈርጁ አካላት በውል ሊገነዘቡት ይገባል።

በኅብረታዊ ሥራ እና አደረጃጀት ውስጥ ለኖረች ፤አሁንም እኖረች ላለችው ቅድስት ቤተ ክርስያናችን ወደ ተግባር የተለወጠ፣በጥበብ የታገዘ ግኙኝነትን በመፍጠር የራስንም ሆነ የቤተ ክርስቲያንን ሕልውና መጠበቅ ከባድ አይደለም። ምክንያቱም የነበረውን አስፍቶ እና አጠንክሮ ማስቀጠል እንጂ አዲስ ሥራ አይጠበቅምና ነው። አሁን ዐቢይ ጉዳይ የሚሆነው እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን ልጅ ከከተማ እስከ ገጠር ፤ከሀገር ውስጥ እስከ ውጪው ዓለም "እንደ አንድ ልብ አሳቢ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ" ሆኖ መገኘት የግድ ነው። ቅዱስ ዳዊት በመዝሙሩ "ወንድሞች በኅብረት ቢቀመጡ ፥ እነሆ መልካም ነው ፥ እነሆም ያማረ ነው።" መዝ ፻፴፫፥፩ እንዳለው የቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆች ኅብረት እጅግ የሚያስፈልግበት ጊዜ ነውና ቸል ሊባል አይገባም።

ዛሬ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ለመታደግ ልጆች የአባቶቻቸውን ቃል ሊሰሙ ይገባል። አባቶች ለልጆች ጆሮአቸውን ሊሰጡ ይገባል። ወደ ጎንም ሆነ በተዋረዳዊው ሠንሠለት ውስጥ በመናበብ፣ በመታዘዝ እና በመቀባበል ለጠነከረ አደረጃጀት በቅድሚያ ወደ አንድነት መምጣት ከእያንዳንዱ የሚጠበቅ ክርስቲያናዊ ግዴታ ነው። ሁሉም ባለበት የዕድሜ፣ የዕውቀት ፤እና የሙያ ደረጃ ለእናት ቤተ ክርስቲያን በአንድነት መቆም ይጠበቅበታል።

ቤተ ክርስቲያን ዘር ቀለም፣ ዕድሜ እና ሙያ ሳይለይ በሚፈጠር ኅብረት ውስጥ ጎልታ ልትታይ የእያንዳንዱ ክርስቲያን የቤት ሥራ ሊሆን ይገባል። በየሙያ ዘርፉ ያሉ የቤተ ክርስቲያን ልጆች፣ በየትኛውም የመንግሥት መዋቅር ላይ ያሉ የቤተ ክርስቲያን ልጆች ከቤተ ክርስቲያን ፣ ከአባቶች ጎን መቆም በኅብረት መሥራት ፣ ባሉበት ቦታ ስለ ቤተ ክርስቲያን ክብር መቆም ዘመኑ የሚጠይቀው ክርስቲያናዊ ግዴታ ነው። "ድር ቢያብር አንበሳ ያሥር" እንዳለ የሀገሬ ሰው ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን የነገ ሕልውና የቤተ ክርስቲያንን አደረጃጀት አስፋፍቶ እና አጥብቆ መጓዝ ያስፈልጋል።

# ከሶማሌ እስከ ጉራፈርዳ...

በካሣሁን ለምለሙ

ቤተ ክርስቲያን በፀረ ክርስቲያን ኀይሎች ትላንት ተፈትናለች፤ ዛሬም እየተፈተነች ትገኛለች። ታግለው ከማይጥሏት ገጥመው ከማያሸንፏት ጋር ግብግብ የገጠሙት እነዚህ ኀይሎች የመውጊያውን ብረት ቢቃወሙ ለነሱ ይብስባቸው ሆናል እንጅ ቤተ ክርስቲያን የኋላ ኋላ ማሸነፏ እንደማይቀር ታሪክ ምስክር ነው። ክርስቲያኖችን በመግደልና በማሳደድ አካላዊ ዕረፍት ይነሷቸው እንደሆን እንጅ ዘለዓለማዊ የሆነውን መንፈሳዊ ዕረፍትን ግን አይነሷቸውም። ክርስቲያኖችን እንደ ክፉ አውሬ እያደኑ መግደል ዛሬ የተጀመረ ሳይሆን ውሎ ያደረ አረመኔያዊ ተግባር ቢሆንም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እያየነው ያለው ደግሞ ተደጋጋሚና ለሰሚው ግራ የሚያጋባ ሆኗል።

በቤተክርስቲያንና በክርስቲያኖች ላይ እየደረሰ ያለው ተደጋጋሚ ጥቃት እንዲቆም ቤተክርስቲያኗ ለመንግሥት በተደጋገሚ ጥያቄ ብታቀርብም በጉልህ የታየ መፍትሔ ባለመገኘቱ ፀረ ክርስቲያን ኀይሎች የልበ ልብ እየተሰማቸው በተደጋጋሚ እጅግ አስከፊ ጥቃት እየፈጸሙ ነው። ከዚህ ቀደም ከተለያዩ መረጃዎች ማወቅ እንደተቻለው በክርስቲያኖች ላይ የደረሰው ጥቃት በአብዛኛው በሶማሌ፣ በኦሮምያ፣ በደቡብ እንዲሁም በቤንሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልሎች ነው።

ሰሞኑን በደቡብ ክልል በቤንች ሸኮ ዞን ጉራፈርዳ ወረዳ፣ በኦሮምያ ክልል ምዕራብ ወለጋ ዞን ጉሊሶ ወረዳ ዋጋ ቃንቃ ቀበሌ እንዲሁም ቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል ዞን ቡለንና ወምበራ ወረዳዎች ታጣቂዎች በፈጸሙት ጥቃት በርካታ ክርስቲያኖች መገደላቸውን፣መቁሰላቸውን፣ መሰደዳቸውን እንዲሁም ሀብት ንብረታቸው መቃጠሉንና መዘረፉን አስመልክቶ ጥቅምት ፳፬ ቀን ፳፻፲፫ ዓ/ም ቅዱስ ሲኖዶስ መግለጫ አውጥቷል። ቅዱስ ሲኖዶስ በመግለጫው በቅርቡ ጥቅምት ፳፪ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም በኦሮምያ ክልል ምዕራብ ወለጋ እና በደቡብ ክልል ጉራፈርዳ ወርዳ እንዲሁም በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል ዞን ምንም ዓይነት የፖለቲካ አመለካከት የሌላቸውና ማልደው በመነሳት አምሽተው በመግባት ምድርን ቆፍረውና አርሰው፣ ዘርተውና አጭደው፣ በድካም ኑሮአቸውን የሚገፉ ንጹሓን ምእመናን ሽማግሌዎች፣ ሴቶችና ሕፃናት ጭምር ሳይቀሩ የጅምላ ጭፍጨፋ በማካሄድ ሕይወታቸው እንዲያልፍ መደረጉ እንዳሳዘነው አስታውቋል። በተለይ የጉራፈርዳንና የምዕራብ ወለጋን ጥቃት የቅዱስ ሲኖዶስ ምልአተ ጉባኤ ዓመታዊ ስብሰባ ላይ እያለ የሰማው መሆኑን ጠቅሶ ቅዱስ ሲኖዶስና ቤተ ክርስቲያን በእጅጉ ያሳዘነ ኢ-ሰብአዊ ድርጊት በመሆኑ ድርጊቱን አውግዟል።

**ከወረዳው አጠቃላይ ተፈናቃዮች ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ኦርቶዶክሳውያን ምእመናን ሲሆኑ ሀገረ ስብከቱም ምእመናኑ በጸጥታ ስጋት መፈናቀላቸው አሳስቦት ከፌዴራል መንግሥት ጀምሮ በየደረጃው ካሉ የመንግሥት አካላት ድጋፍና እገዛ እንዲደረግና ወደ ቀደመ ቀያቸው በቶሎ እንዲመለሱ ጠይቋል።**

"አላስፈላጊ በሆነ ምክንያት በግፍ ለተገደሉትና ሕይወታቸውን ላጡ ምእመናን በቤተ ክርስቲያናችን ስም ልባዊ ሐዘናችንን እየገለጽን ዳግም እንዲህ ዓይነት ኢ-ሰብአዊ ድርጊት እንዳይፈጸም መንግሥት ለዜጐች አስፈላጊውን ጥበቃ እንዲያደርግ ወንጀለኞችንም ለፍርድ እንዲያቀርብ" ሲል ቅዱስ ሲኖዶስ አሳስቧል። መላው ኢትዮጵያውያንንም በቀጣይ ለጋራ ሰላምና አንድነት እንዲቆሙ ጥሪ አቅርቧል።

በደቡብ ክልል ቤንች ሸኮ ዞን ጉራፈርዳ ወረዳ በንጹሓን ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች ላይ የተፈጸመውን ጥቃት በተመለከተ የሸካ ቤንች ሸኮ እና ምዕራብ ኦሞ አህጉረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ መልአከ ጽዮን አባ ሚካኤል ገብረ ማርያም የሚከተለውን መረጃ ለዝግጅት ክፍላችን በስልክ ነግረውናል።

በእርሳቸው መርጃ መሠረት በአካባቢው የሚኖሩ ኦርቶዶክሳውያን ምእመናንን ጨምሮ ከአምስት ሺህ በላይ ኢትዮጵያውያን በጸጥታ ችግር ምክንያት ከጉራፈርዳ ወረዳ ተፈናቅለዋል። ጥቃት በተፈጸመበት ወቅት ከተፈናቀሉት ምእመናን ይልቅ አሁን በአካባቢው መጠነኛ መረጋጋት በታየበት ወቅት የተፈናቀሉት ምእመናን ቁጥር እንደሚበልጥ አስረድተዋል። ከወረዳው አጠቃላይ ተፈናቃዮች ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ኦርቶዶክሳውያን ምእመናን ሲሆኑ ሀገረ ስብከቱም ምእመናኑ በጸጥታ ስጋት መፈናቀላቸው አሳስቦት ከፌዴራል መንግሥት ጀምሮ በየደረጃው ካሉ የመንግሥት አካላት ድጋፍና እገዛ እንዲደረግና ወደ ቀደመ ቀያቸው በቶሎ እንዲመለሱ ጠይቋል።

**የወረዳና የዞን የመንግሥት አመራሮች ችግሩ ከደረሰ በኋላ ተጨማሪ ጥቃት እንዳይደርስ ጥንቃቄ የተሞላበት ሥራ ሲሠሩ ቆይተዋል። ለዚህ ሥራቸውም ሀገረ ስብከቱ ዕውቅና ሰጥቷል።**

ምንም እንኳን በአብያተ ክርስቲያናቱ ላይ የደረሰ ጥቃት ባይኖርም ለደኅንነታቸው ሲባል ግን ሦስት አብያተ ክርስቲያናት ያህል መደበኛ አገልግሎት እንዳይሰጡ ተዘግተዋል። በአካባቢው ታጣቂዎች በፈጸሙት ጥቃት የሞቱ ኦርቶዶክሳውያን ምእመናን ከአሥራ አምስት በላይ ናቸው ተብሎ ቀደም ሲል የተነገረ ሲሆን በዚህ ሰዓት በትክክል በተደረገ ጥናት መሠረት ግን ዐሥር ያህል ብቻ እንደሞቱ ማረጋገጥ ተችሏል። ቁጥራቸው በውል የታወቀ ምእመናን ደግሞ ከባድና ቀላል የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል። በአካባቢው ባሉ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት በማገልገል ላይ የነበሩ ካህናት እንዲሁ በጸጥታ ሥጋት አካባቢውን ለቀው ወጥተዋል።

በቀጣይም በአካባቢው በቤተ ክርስቲያን፣ በምእመናን እንዲሁም በሌሎች ኢትዮጵያውያን ላይ ታጣቂ ቡድኑ ተጨማሪ ጥቃት ለማድረስ ቅድመ ዝግጅት እያደረገ እንደሆነ የሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ ያመለክታል። በመሆኑም ለመንግሥትና ለሚመለከታቸው አካላት ከማሳወቅ በተጨማሪ ምእመናን ራሳቸውንና ቤተ ክርስቲያናቸውን ነቅተው እንዲጠብቁ መልእክት ተላልፏል።

የወረዳና የዞን የመንግሥት አመራሮች ችግሩ ከደረሰ በኋላ ተጨማሪ ጥቃት እንዳይደርስ ጥንቃቄ የተሞላበት ሥራ ሲሠሩ ቆይተዋል። ለዚህ ሥራቸውም ሀገረ ስብከቱ ዕውቅና ሰጥቷል። ወረዳው ከዞን አመራሮች እንዲሁም ከክልል የመንግሥት ኀላፊዎች ጋር ተቀናጅቶ ሲሠራም ቆይቷል። ሆኖም ግን የክልሉ መንግሥት አንዳንድ የዞንና የወረዳ አመራሮችን ‹‹ኃላፊነታችሁን ቀድማችሁ ባለመወጣታችሁ ነው የጸጥታ ችግር የተፈጠረው›› በማለት በተጠርጣሪነት የመያዝ ሥራ እየሠራ ነው። በአሁኑ ሰዓት አካባቢው በክልልና ፌዴራል መንግሥት ኮማንድ ፖስት ሥር ያለ ሲሆን የዞንና የክልሉ መንግሥት በጋራ ተፈናቃዮችን ወደ ቀደመ ቀያቸው ለመመለስ ጥረት እያደረጉ ይገኛሉ። በተለይ የክልሉ መንግሥት ለተፈናቃዮች አስፈላጊ ነው ያለውን ሁሉ ሰብአዊ ድጋፍ በማድረግ ላይ ይገኛል። ይህ መልካም ጅምርና ለሌሎች አካባቢዎች ምሳሌ የሚሆን ተግባር ነው።

ለጥበቃ የማያመቹ አንዳንድ አካባቢዎች ካልሆኑ በስተቀር የፌዴራል መንግሥት በቂ ጥበቃ ለየአብያተ ክርስቲያናቱ መድቦ ሃያ አራት ሰዓት ሙሉ በሚያስመሰግን ሁኔታ ጥበቃ እየተደረገላቸው ነው። ሀገረ ስብከቱም ለተፈናቀሉ ምእመናን የማጽናኛ ትምህርት ከመስጠት በተጨማሪ የዕለት ደራሽ ምግቦችንና ቁሳቁስ ድጋፍ አድርጓል።

በጥሬ ገንዘብ ድጋፍ ለማድረግም ከአንድ መቶ ሺህ ብር በላይ ተሰብስቦ በቀጥታ ድጋፍ ለማድረግ ቅድመ ዝግጅት ተጠናቋል፡፡

የተፈናቀሉ ኦርቶዶክሳውያን ምእመናንና ሌሎች ኢትዮጵያውያን በአንድ ድንኳን ውስጥ ተጠልለው ይገኛሉ፡፡ የሀገረ ስብከቱ አገልጋዮች ኦርቶዶክሳውያን ምእመናንን ብቻ ለይተው ሳይሆን ሁሉንም የማጽናናት ሥራ ሠርተዋል፡፡ ሀገረ ስብከቱ ለምእመናንና ለሌሎች ኢትዮጵያውያን እያደረገ ያለው ሁሉን አቀፍ ድጋፍ ሃይማኖትን የለየ ባለመሆኑ ይህንን ማድረጉ ቤተ ክርስቲያን በሌሎች አማንያን ዘንድ በጥሩ እይታ እንድትታይና የበለጠ እንድትከበር አድርጓታል፡፡

በሚከናወነው የሰብአዊ ድጋፍ እርዳታ ሁሉ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ሕዝቅኤል ከጎናቸው እንደነበሩ ሥራ አስኪያጁ ተናግረዋል፡፡ ብፁዕነታቸው ዓመታዊ የቅዱስ ሲኖዶስ ስብሰባ ላይ በመሆናቸው ምክንያት በቦታው ባይገኙም ስልክ እየደወሉ መመሪያና አቅጣጫ ከመስጠት በተጨማሪ አባታዊ የማጽናኛ ቃል አድርሰዋል፡፡ ሥራ አስኪያጁ ባስተላለፉት መልእክት "ግፍንና በደልን ማለፍ የምንችለው እግዚአብሔርን በጸሎት በመጠየቅ ነው፡፡ ሀገረ ስብከቱ ኦርቶዶክሳውያን ምእመናን ወደቀደመ ቀያቸው ለመመለስ ሰብአዊ ድጋፍ ከማድረግ በተጨማሪ እግዚአብሔርን በጸሎት እየለመነ ነው፡፡ በአካባቢው ብሎም በኢትዮጵያ እንዲህ ዓይነት ክፉ ጊዜ እንዳይመጣ፤ ወላጆችን ነጥቆ ልጆችን ያለአሳዳጊ የሚያስቀር ልጆችን ነጥቆ ወላጆችን ያለቀባሪ ጧሪ የሚያስቀር ዘመን ተመልሶ እንዳይመጣ ለፈጣሪም ለመንግሥትም አቤት እንበል" ብለዋል፡፡

"የተፈናቀሉ ምእመናንም እኛን የሃይማኖት አባቶችን እንዲሁም ከፌዴራል እስከ ዞንና ወረዳ ያሉ የመንግሥት ባለሥልጣናት የሚሉትን በመስማት ወደቀያቸው መመለስ አለባቸው እንላለን፡፡ ምእመናን ወደቀያቸው እስኪመለሱ ድረስ ደስ በሚል ሁኔታ መንግሥት አስፈላጊውን ሁሉ ድጋፍ በማድረግ እንዳይራቡና እንዳያዝኑ እያደረገ ይገኛል፡፡ ምእመናንም ሁሉም ኢትዮጵያዊ ከጎናቸው መሆኑን አውቀው በሰላም ወደ ቀያቸው እንዲመለሱና የተለመደ ኑሯቸውን እንዲጀምሩ አባታዊ መልእክት እናስተላልፋለን፡፡"

ችግር አሁንም በቀጣይ ሊኖር ስለሚችል ምእመናን ሃይማኖታቸውንና ቤተ ክርስቲያናቸውን ነቅተው መጠበቅ ይኖርባቸዋል፡፡ ምእመናንም ጉዳት ለደረሰባቸው አስፈላጊውን እገዛ በማድረግ ጊዜውን ተጋግዞ ማለፍ ቢቻል መልካም ነው፡፡ መንግሥትም መሰል የጸጥታ ችግሮች ዳግም እንዳይከሰቱ ቀድሞ መሥራት ይኖርበታል፡፡ የዜጎችን ደኅንነትና የሕይወት ዋስትና የማረጋገጥ ኀላፊነት ያለበት መንግሥት መሆኑን አውቆ መሠራት ያለባቸውን ሁሉ ቀድሞ በመሥራት የዜጎችን በሕይወት የመኖር መብት ሊያረጋግጥላቸው ይገባል፡፡

ዝግጅት ክፍላችን በጉዳዩ ዙሪያ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ለቤንች ሸኮ ዞን የጸጥታ ዘርፍ ኀላፊ ኮማንደር ምናሉና ለዞኑ አስተዳዳሪ አቶ ፍቅሬ አማን ስልክ የደወልንላቸው ቢሆንም ሁለቱ የመንግሥት ባለሥልጣናት ስልክ ባለማንሳታቸው የእነርሱን ምላሽ ማካተት አልቻልንም፡፡

**ሀገረ ስብከቱ ለምእመናንና ለሌሎች ኢትዮጵያውያን እያደረገ ያለው ሁሉን አቀፍ ድጋፍ ሃይማኖትን የለየ ባለመሆኑ ይህንን ማድረጉ ቤተ ክርስቲያን በሌሎች አማንያን ዘንድ በጥሩ እይታ እንድትታይና የበለጠ እንድትከበር አድርጓታል፡፡**

# “በውጪው ዓለም ቤተ ክርስቲያን ተመሠረተች ሳይሆን ተስፋፋች እላለሁ”

*-መልአከ ገነት በለጠ ይረፉ*

**ክፍል አንድ**



መልአከ ገነት በለጠ ይረፉ

**በመጽሐፈ ሲራክ**

*የተወደዳችሁ አንባብያን በዛሬው የቤተ አብርሃም ዓምድ ዝግጅታችን ይዘንላችሁ የቀረብነው በሰሜን አሜሪካ የሴንት ሊውስ ደብረ ናዝሬት ቅድስት ማርያም እና ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪና የኦሃዮ ሀገረ ስብከት ዋና ጸሐፊ የሆኑትን መልአከ ገነት በለጠ ይረፉን ነው።*

*በመንፈሳዊ አገልግሎት ከገጠር እስከ ከተማ፣ ከኢትዮጵያ እስከ አፍሪካ፣ ከአውሮፓ እስከ አሜሪካ በብዙ አድባራት በተለያየ ኃላፊነት ተመድበው ውጤታማ ሥራ ሠርተዋል።*

*እኛም በ፳፻፲፫ ዓ.ም ፴፱ኛው ዓለም አቀፍ የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ላይ ሀገረ ስብከታቸውን ወክለው ኢትዮጵያ በመጡበት ጊዜ አግኝተናቸው ከልጅነት እስከ እውቀት ያላቸውን የሕይወት ተሞክሮ (የሥራ ልምድ እንዲያካፍሉን የአብርሃም ቤት እንግዳ አድርገናቸዋል እነሆ፦*

***ስምዐ ጽድቅ፦*** በቅድሚያ ጥሪያችንን አክብረውና ለቃለ ምልልስ ፈቃደኛ ሆነው ስለተገኙልን በልዑል እግዚአብሔር ስም እናመሰግናለን።

***መልአከ ገነት በለጠ ይረፉ፦*** እኔም አክብራችሁ ሐሳቤን እንድሰጥ የሕይወት ተሞክሮዬንም ለሌሎች እንዳካፍል ለቃለ ምልልስ ስለጋበዛችሁኝ አመሰግናለሁ የምሰጠውም ሐሳብ የሚጠቅም እንዲሆንልኝ እመኛለሁ።

***ስምዐ ጽድቅ፦*** በመጀመሪያ የት ተወለዱ? ወላጆችዎ ማን ይባላሉ? የትስ ተማሩ?

***መልአከ ገነት በለጠ፦*** የተወለድኩት በ፲፱፻፷ ዓ.ም በኦሮምያ ክልል አሩሲ፣ ሥሬ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን አጥቢያ ነው። አባቴ ሊቀ አበው ይረፉ ደንባው ይባላሉ አሁን በሕይወተ ሥጋ የሉም፣ እናቴ እማሆይ በቀለች ለሽበሉ ይባላሉ በሕይወት አሉ። ወደ መንፈሳዊ ት/ቤት የገባሁት በሕፃንነት ዕድሜዬ ነው ለዚህም ምክንያቱ ደግሞ ታላላቅ ወንድሞቼ ሁሉ ካህናት እና ዲያቆናት ስለነበሩ የእነርሱን ፈለግ በመከተል ነው።

የቃልና የንባብ ትምህርት እስከ ግብረ ዲቁና ሥሬ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ከቆሞስ አባ ሀረገ ወይን (አቡነ ሰላማ) ዘንድ ተምሬ በ፲፱፻፸፫ ዓመተ ምሕረት ከብፁዕ አቡነ ኤፍሬም የዲቁና ክህነት በመቀበል በይመና ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን በዲቁና አገለግያለሁ።

ውዳሴ ማርያም ዜማ መስተጋብዕ ሠለስት አርያምን የተማርኩት ጀጁ ቅዱስ በዓለ ወልድ ቤተ ክርስቲያን ከሊቀ ልሳናት ነቅዓ ጥበብ ቸኮል ዘንድ ነው። ሥርዓተ ቅዳሴን የተማርኩት ቀጨኔ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ከየኔታ

ሙሴ ዘንድ ነው:: ሰዓታት የተማርኩት ምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ገዳም ከታላቅ ወንድሜ ሊቀ መዘምራን ፀጋዬ ይረፉ ዘንድ ነው:: በዓለማዊ ትምህርት ከአልፋ የርቀት ትምህርት ኮሌጅ በሒሳብ አያያዝና ማኔጅመት የትምህርት ዘርፍ ተምሬ ተመርቄአለሁ::

***ስምዐ ጽድቅ፦*** የጀመሩትን መንፈሳዊ አገልግሎት በመደበኛነት ያገለገሉባቸውን ቦታዎች ቢገልጹልን?

***መልአከ ገነት በለጠ፦*** እውነት ነው ቅዱስ ጳውሎስ “ያጸናኝን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን አመሰግነዋለሁ፤ ለመልእክቱ ሾሞ ታማኝ አድርጎኛልና“ ፩ኛ ጢሞ ፩፥፲፪ ብሎ ለጢሞቴዎስ እንደነገረው እግዚአብሔር ፈቅዶልኝ መንፈሳዊ አገልግሎት የጀመርኩት እጅግ ሕፃን ሳለሁ ነው:: እግዚአብሔር አባቴ ቤተ ክርስቲያን እናቴ አገልግሎቷም ጥማቴ ብዬ በሀገሬ በኢትዮጵያ ፤ከሀገር ውጪ ከአፍሪካ እስከ አሜሪካ አውሮፓንና ካናዳን ጨምሮ በአለችኝ ትንሽ እውቀትና በተሰጠኝ ፀጋ መጠን በቅዳሴ፣ በዝማሬ፣ በስብከተ ወንጌል፣ በፀሐፊነትና በአስተዳዳሪነት አገልግያለሁ::

**በውጪ ሀገር አንድ ካህን ለቤተ ክርስቲያን የሚሰጠው መንፈሳዊ አገልግሎት ዘርፈ ብዙ ነው በውስጥ ገብቶ ይቀድሳል፣ በዓውደ ምህረት ቆሞ ያስተምራል፣ በቅኔ ማኅሌቱ ያገለግላል ፣ ያፀዳል : ያነጥፋል፣ ንስሐ አባት ነው ይጠብቃል፣ አማካሪ ነው አስታራቂ ሽማግሌም ነው። በእውነት ጨው መሆኑ የሚታይበት አገልጋይነቱ በትክክል የሚረጋገጥበት ነው።**

በቀጨኔ ደብረ ሰላም መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ደጅ እየጠናሁ የቅዳሴ ትምህርት ከተማርሁ በኂላ የኮተቤ መካነ ቅዱሳን ኢያቄም ወሐና ቤተ ክርስቲያን ሲቋቋም የቃል ኪዳኑ ታቦታ ከቀጨኔ ደብረ ሰላም መድኃኔ ዓለም ሄዶ ፫ኛው ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ቅዳሴ ቤቱን ሲያከብሩ የመጀመሪያው ዲያቆን ሆኜ ገባሁ:: በዚያው ቀርቼም በዲቁና፣ በሰባኬ ወንጌልነት በዋና ጸሐፊነት አገልግያለሁ::

ከመካነ ሰላም ኢያቄም ወሐና ቤተ ክርስቲያን ወደ ደብረ ይባቤ ቅዱስ ያሬድ ቤተ ክርስቲያን በዋና ፀሐፊነት ተዛውሬ በወቅቱ ሰባኬ ወንጌል የነበሩት አባት ቆሞስ አባ መልአኩ ጌታነህ (የአሁኑ ብፁዕ አቡነ ፋኑኤል) ም/ አስተዳዳሪ ሆነው ሲሾሙ እኔ በምትካቸው የስብከተ ወንጌል ኃላፊ ሆኜ ተመድቤ አገልግያለሁ:: ከደብረ ይባቤ ቅዱስ ያሬድ ቤተ ክርስቲያን ወደ እንጦጦ መንበረ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ተዘዋውሬ በጊዜው የደብሩ ሰባኬ ወንጌል የነበሩት አባ አፈወርቅ ወደ ውጪ ሀገር ሲሄዱ በእሳቸው ቦታ በሰባኬ ወንጌልነት ለአንድ ወር እንደሰራሁ የደብረ ይባቤ ቅዱስ ያሬድ ቤተ ክርስቲያን ካህናትና ምእመናን ዝውውሩን በመቃወም ይመለሱልን ብለው ቤተ ክህነቱን ስለጠየቁ ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ደብረ ይባቤ ቅዱስ ያሬድ ቤተ ክርስቲያን ተመልሼ በስብከተ ወንጌል ኃላፊነት ያገለገልኩ ሲሆን ቅዱስ ጋብቻዬንም የፈጸምኩት በዚሁ ደብር በዚያን ጊዜ ነው::

ከደብረ ይባቤ ቅዱስ ያሬድ ቤተ ክርስቲያን ወደ ጥንታዊውና ታሪካዊው የየካ ደብረ ሳህል ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ተዛውሬ በዋና ጸሓፊነት አገልግያለሁ:: ፈቃደ እግዚአብሔር ሆኖ በሀገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ የተሰራው የካራ ቅዱስ ፋኑኤል ቤተ ክርስቲያን ሲቋቋም የመጀመሪያ አስተዳዳሪ ሆኜ የቃል ኪዳኑን ታቦት ከጠቅላይ ቤተ ክህነት ተቀብዬ አዲስ ቤተ ክርስቲያን ፤አዲስ ቦታ፤አዲስ አለቃ ሆኜ አገልግያለሁ::

በመቀጠል ወደ ሳሪስ አዲስ አምባ ደብረ ገነት ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን በአስተዳዳሪነት ተዘዋወርኩ:: የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ በካህናቱ አንድነት በሕዝቡም አስተዋይነት በደብሩ ላይ ውጤታማ ሥራ የሠራሁበት፤ ብዙ በረከት ያገኘሁበት ቦታ ነው:: በስብከተ ወንጌልና በመልካም አስተዳደር ከአዲስ አበባ አድባራት የተሻለ ውጤት በማምጣት ተሸላሚ ለመሆን የበቃሁበት ደብር ነው እግዚአብሔር ቢፈቅድ መካነ ዕረፍቴ እንደሚሆን ይሰማኛል:: ከሳሪስ አዲስ አምባ ደብረ ገነት ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ወደ ገርጂ ደብረ ገነት ቅዱስ

ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በአስተዳዳሪነት ተመድቤ ነበር፤ ነገር ግን የኪዳነ ምሕረት ካህናትና ምእመናን ቅያሬውን በመቃወም ለቅዱስ ፓትርያሪኩ ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት በማግኘቱ ለሁለተኛ ጊዜ በአዲስ አምባ ደብረ ገነት ኪዳነ ምህረት ቤተ ክርስቲያን በአስተዳዳሪነት አገልግያለሁ።

ሳሪስ አዲስ አምባ ደብረ ገነት ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን እያለሁ በተከታታይ የሰሜን አሜሪካ የዋሽንግተን ሲያትል ቅዱስ አማኑኤል ቤተ ክርስቲያን፣ የስዊድን እስቶክሆልም መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን በአስተዳዳሪነት ተመድቤ ነበር። ነገር ግን ጉዞው ሳይሳካ ቀረ። በሦስተኛው ግን በጣሊያን ሚላኖ የፈለገ ሰላም ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ ሆኜ ተመደብኩ ነገሩ ተሳካና ወደ ጣሊያን ሄጄ ለሁለት አመታት ያህል በአስተዳዳሪነት አገልግያለሁ።

***ስምዐ ጽድቅ፦*** የውጪ ሀገር ጉዞ ለሁለት ጊዜ ተጀምሮ ከቀረ በኋላ በሦስተኛው ተሳክቶ ወደ ጣሊያን እንደሄዱ ነግረውናል በዚያ ያለውን አገልግሎት እንዴት አገኙት ?

***መልአከ ገነት በለጠ፦*** እንግዲህ አስቀድሞ የተመደብኩበት የውጪ ሀገር ጉዞ ያልተሳካው ለበጎ መሆኑን ሁሉንም ከአየሁት በኋላ በሚገባ ተረድቻለሁ። በተለይ ደግሞ ሰሜን አሜሪካ ተመድበሃል ተብዬ ደብዳቤ ደርሶኝ ከምወደው ደብሬና ሕዝቤ መካከል ተነስቼ ቦታውን አስረክቤ ብዙ ተወርቶ ሲቀር አዝኜ ነበር፤ የተሰጠኝም ምክንያት አላሳመነኝም፤ ሰውም ደህና ነገር አልነገረኝም፤ ነገር ግን "ያለ እርሱ ፈቃድ የሚበላ ወይም የሚጠጣ ማነው?" መክ ፪፥፳፭ እንዲል እግዚአብሔር ለእኔ ከእኔ በላይ ስለሚያስብ ነው በማለት ተቀብዬዋለሁ። በእርግጥ ከደብረ ይባቤ ቅዱስ ያሬድ ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪነት ወደ ጣሊያን ሚላኖ ፈለገ ሰላም ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ተመድበሃል የሚል ደብዳቤ ሲደርሰኝ እንደ በፊቱ ሊሆን ይችላል የሚል ግምት ነበረኝ ነገር ግን በአጭር ጊዜ ውስጥ ተፈጽሞ እንድወጣ ተደረገ።

በእውነት በቦታው ስደርስ ዲያቆናቱ፣ መዘምራኑና ምእመናኑ ነበሩ በፍቅር የተቀበሉኝ። የአባቶቼ አምላክ እግዚአብሔርም ስለተከተለኝ ሰበካ ጉባኤው፣ ዲያቆናቱ፣ መዘምራኑና ምዕመናኑ ሁሉ የምላቸውን የሚሰሙ ሆኑልኝ፣ እኔም እነርሱን በሚገባ እሰማለሁ በፍፁም መተባበር በአንድነትና በፍቅር ሆነን መንፈሳዊ አገልግሎቱን በማጠናከር፣ ወጣቱን በማስተባበር ፣ሕዝቡንም በማስተማር እና ስልጠና በመስጠት ለሁለት ዓመታት ውጤታማ ሥራ ለመሥራት ችያለሁ።

ምንም እንኳ የተመደብኩት ሚላኖ ፈለገ ሰላም ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ቢሆንም በአካባቢው በሚገኙ ከተሞች የሚኖሩትንም ምእመናን ለማገልገል እንፋጠን ነበር። ዛሬ ቤተ ክርስቲያን ሆነው አገልግሎት እየሰጡ ያሉ ቦታዎች በዚያን ጊዜ በጽዋ ማኅበር ስም ያሰባሰብናቸው ናቸው። በወቅቱ በጣሊያን ሀገር ሁለት አብያተ ክርስቲያናት ብቻ ነበሩ የሚላኖ ፈለገ ሰላም ቅዱስ ገብርኤልና የሮም ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ናቸው። ዛሬ እግዚአብሔር ይመስገን በርካታ ሆነዋል። ከእኔ በፊት የነበሩት ንቡረ እድ ኃይለ ልዑል ወልደ ገሪማም ብዙ ሠርተዋል።

በውጪ ሀገር አንድ ካህን ለቤተ ክርስቲያን የሚሰጠው መንፈሳዊ አገልግሎት ዘርፈ ብዙ ነው በውስጥ ገብቶ ይቀድሳል፣ በዓውደ ምህረት ቆሞ ያስተምራል ፣በቅኔ ማኅሌቱ ያገለግላል፣ ያፀዳል: ያነጥፋል፣ ንስሐ አባት ነው ይጠብቃል፣ አማካሪ ነው አስታራቂ ሽማግሌም ነው። በእውነት ጨው መሆኑ የሚታይበት አገልጋይነቱ በትክክል የሚረጋገጥበት ነው።

***ስምዐ ጽድቅ፦*** ወደ አሜሪካን ሀገር እንዴት ሄዱ? በዚያ ያለ የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት እንዴት ጀመሩ?

***መልአከ ገነት በለጠ፦*** ለሥራ ተመድቤ ወደ ጣሊያን ሚላኖ ስሄድ የቃል ኪዳን ባለቤቴንና ሕፃናት ልጆቼን ሀገር ቤት ጥያቸው ነበር የሄድኩት። ነገር ግን ጊዜው እየገፋ ሲሄድ የቤተሰቤ ናፍቆት እንዲሁም በውጭ ሀገር ያለው የብቸኝነት ኑሮ እየከበደኝ ሄደ። ከኔ ጋር መጥተው አብረን እንድንኖር ይደረግልኝ ዘንድ በተደጋጋሚ ብጠይቅም ዛሬ ነገ በሚል ብዙ ጊዜ ወሰደ፤ እኔም "ከሙክት መካከል ከሚውል ቀበሮ ከልጆቹ ጋር የሚጭር ዶሮ ይበልጣል "እንዲሉ ከእግዚአብሔር የተሰጡኝ አደራዎቼ ናቸውና

ስለ እነርሱ ስል ወደ አሜሪካን ጉዞ አደረኩ። አሜሪካን የገባሁት በእነርሱ ምክንያት ነው።

አሁን የማገለግልበት የሴንት ሊውስ ደብረ ናዝሬት ቅደስት ማርያምና ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖታቸው በፀና ምግባራቸው በቀና በጥቂት ምእመናን የተቋቋመ ነው። እኔም አገልግሎት የጀመርኩት በዚያ ነው። ከአንድ ዲያቆን ጋር በመሆን በኪራይ ቤተ መቅደስ ብዙ ጊዜ ቀድሻለሁ። እግዚአብሔር ይመስገን ዛሬ ተጨማሪ ካህናት እና በርካታ ዲያቆናት አሉን ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ገዝተናል፤ ዕዳውንም ከፍለን ጨርሰናል ፤የሕዝቡም ቁጥር እጅግ በዝቷል። ሌላው በዚያው የተወለዱ እና ቋንቋችንን የማያውቁ ሕፃናት ግብረ ዲቁና ተምረው ክህነት ተቀብለው ያገለግላሉ፤ ዜማውን በግእዝ ንባቡን ደግሞ በእንግሊዘኛ ይጠቀማሉ ይልቁንም በሀገራችን ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን በማገልገል የኖሩ የማኅበረ ቅዱሳን አባላት የሆኑ ዲያቆናት በሥራና በትምህርት ስለመጡ የቤተ ክርስቲያኑን አገልግሎት ከፍ አድርገውታል።

***ስምዐ ጽድቅ፡*** በአጠቃላይ በሰሜን አሜሪካ የቅድስት ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ምን ይመስላል? እንደ ኦሃዮ ሀገረ ስብከትስ?

***መልአከ ገነት በለጠ፡*** አስቀድሜ እንዳልኩት በውጪ ሀገር ያለው መንፈሳዊ አገልግሎት በሀገር ውስጥ ካለው አገልግሎት የሚለየው በአገልግሎቱ፣ በእምነቱና በሥርዓቱ ሳይሆን በካህናቱና በምእመናኑ ቁጥር ብዛትና ማነስ እንዲሁም በጊዜውና በቦታው ነው። በሀገራችን በብዙ ካህናት የተለመደው አገልግሎት በዚያ አይገኝም። በአንዳንድ ቦታዎች በዛ ያሉ ካህናት ቢኖሩም በአንዳንድ ቦታዎች ደግሞ ቁጥሩ አንድም ሁለትም ሊሆን ይችላል። የምእመናኑም ቁጥር እንደዚያው ነው በኑሮ በሥራ የተወጠረ ከራሱ አልፎ ቤተሰቡን ሀገሩን ቤተ ክርስቲያኑን ለመርዳት የሚሮጥ ጊዜ የሌለው ይሆናል። ቢሆንም ግን በትንቢተ ኤርሚያስ "በውኑ ኢትዮጵያዊ መልኩን ወይስ ነብር ዝንጉርጉርነቱን ይለውጥ ዘንድ ይችላልን?" ት.ኤር ፲፫፥፳፫ እንደተባለው ተዋህዶ ሃይማኖቱን ቤተ ክርስቲያን እናቱን ይወዳል። ምእመናኑ በአንዳንድ ቦታዎች ቁጥራቸው ትንሽ ሆኖ ነገር ግን ከፍተኛ ሥራ ሠርተው ይታያሉ። በሰሜን አሜሪካ በትልልቁ ግዛቶችና ከተሞች ትልልቅ አብያተ ክርስቲያናት እንዲሁም ብዙ ካህናት፣ዲያቆናትና መምህራንም አሉ።

እኔ በአለሁበት ኦሃዮና አካባቢው ሀገረ ስብከት አስራ ስምንት አብያተ ክርስቲያናት አሉ። ሁሉም ራሱን የቻለ ህንፃ ቤተ ክርስቲያን አላቸው። በሀገራችን ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን በምእመናን አስተዋጽኦ ይሠራል በውጭ ሀገር ግን እንደዚህ አይደለም መጀመሪያ በኪራይ ወይም ደግሞ ሕንፃው ተገዝቶ ነው አገልግሎቱ የሚሰጠው። በእርግጥ አንዳንዶች መሬቱን ገዝተው ሕንፃውን የሠሩ አሉ።

***ስምዐ ጽድቅ፡*** አብያተ ክርስቲያናት ከኪራይ ሕንፃ ወጥተው በራሳቸው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ማገልገላቸው ጥሩ ሆኖ ሳለ በኪራይ ሕንፃ ማገልገሉ የሚያስከትለውን ችግር ይግለፁልን?

***መልአከ ገነት በለጠ፡*** የኪራይ ቤት እንኳን ለቤተ ክርስቲያን ለመኖሪያነትም ቢሆን ከባድ ነው ይልቁንም አከራይ የእምነቱ ተከታይ ከአልሆነ፣ እምነቱንና ሥርዓቱን ከአላወቀ አሊያም የሌላ እምነት ተከታይም ከሆነ ብዙ ችግሮች አሉ።

ለምሳሌ ሕንፃውን ግማሽ ቀን አከራይተው ግማሽ ቀን ደግሞ ራሳቸው የሚገለገሉበት ሊሆን ይችላል። እኛ በምንገለገልበት ጊዜ መንበሩን በቋሚነት ዘርግተን ፤የቃል ኪዳኑን ታቦት በቋሚነት ትተን፣ መጋረጃውን ዘርግተን፣ ነዋየ ቅድሳቱን አሟልተን እና በፈለግንበት ሰዓት ከፍተንና ዘግተን ለመገልገል እንቸገራለን። ሰዓት አሳጥሩ ፣ዕጣን አትጠኑ፣ ከበሮ አትምቱ . . . ወዘተ የሚል ሐሳብ ያቀርባሉ። ኪራዩን አቋርጠው ልቀቁ የሚሉበት ጊዜም ይኖራል። በእውነት ኪራይ ሲሆን ችግሩ ብዙ አይነት ነው።

የራስ የሆነ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ሲሆን እንዚህ ችግሮች ሁሉ አይኖሩም። መንፈሳዊ አገልግሎት በተሟላ ሁኔታ በዕለተ ሰንበትም ሆነ በዘወትር በወርኃዊና ዓመታዊ በዓላት መስጠት ይቻላል። ምእመናንም ተረጋግተው ይገለገላሉ፤ ከታቦቱ እስከ ነዋየ ቅድሳቱ በክብር ይቀመጣሉ።

አሁን በሰሜን አሜሪካ የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት በአብዛኛው ማለት ይቻላል ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን የገዙና የሠሩ ናቸው። ከእነዚህ ውስጥ ገንዘቡን ከፍለው የጨረሱ በመክፈልም ላይ የሚገኙ አሉ ከገዙትና ከፍለው ከጨረሱት መካከል አንዱ እኔ ያለሁበት ደብር ነው።

ቤተ ክርስቲያን እንደ ነጋዴ ነግዳ አታተርፍም፤ እንደ ገበሬም አርሳ አታመርትም ትርፎቿና ምርቶቿ ካህናትና ምእመናን ናቸው። ቤተ ክርስቲያን የምትስፋፋው በካህናትና ምእመናን ትብብርና ጥረት ፍቅርና አንድነት ነው። ሃይማኖታቸውን የሚወዱ ክርስቲያኖች ለቤተ ክርስቲያን የሚችሉትን ሁሉ ያደርጋሉ በገንዘባቸው በእውቀታቸው በጉልበታቸው ይታዘዛሉ።

በተለይ ምሳሌ የሚሆናቸው፣ የሚያስተምራቸው መልካም አባት ወይም ካህንና መሪ ከአገኙ ለመልካም ነገር ይሽቀዳደማሉ። ምንጊዜም ቢሆን ከካህናት የሚጠበቀው ብዙ ነገር ነው፤ ብዙ ከተሰጠው ብዙ ይጠበቃልና። ይህ ማለት ግን ከምእመናን የሚጠበቅ ነገር የለም ማለት አይደለም።

***ስምዐ ጽድቅ፦*** የቤተ ክርስቲያን (የክርስትና) ጉዞ በውጭው ዓለም በተለይም እርስዎ በሚገኙበት ሀገረ ስብከት ምን ይመስላል? አመሠራረቷን ጭምር ቢነግሩን።

***መልአከ ገነት በለጠ፦*** በመጀመሪያ እኔ ቤተ ክርስቲያን በውጪ ሀገር ተስፋፋች እንጂ ተመሠረተች የሚል ሐሳብ የለኝም። መሠረቷ ያለው ገዳማቱ አድባራቱ ሊቃውንቱ ካህናቱና ምእመናኑ በአሉበት በኢትዮጵያ ስለሆነ ነው። በውጪ ሀገር በአፍሪካ፣ በአውሮፓ፣ በአሜሪካና በአውስትራልያ፣ በእስያና በካራቢያን ደሴቶች በሌሎችም ቦታዎች ተስፋፍታለች። ለዚህ ደግሞ ብዙ ምክንያቶች ቢኖሩም ከሁሉ በፊት ፈቃደ እግዚአብሔር ነው ብዬ አስባለሁ። የእግዚአብሔር መንገድና ጥበብ ለሰው የተገለጠ አይደለም ቤተ ክርስቲያን በተለያየ ምክንያት ብትቋቋምም አሁን በደረስንበት ላይ ሆነን ስናስበው እግዚአብሔር የወደደውና የፈቀደው ነገር ነው ብዬ አምናለሁ።

የአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት መስፋፋት የመከፋፈል ውጤት ናቸው እላለሁ። በእርግጥ ምክንያቱ ሊለያይ ይችላል። የአስተዳደር፣ የሥርዓት፤ ሰዎች በፖለቲካ አስተሳሰባቸው ሲለያዩ፣ በመንደር፣ በጎሳ፣ በሥልጣንና በጥቅም በሲኖዶስም የተነሳ ሲጋጩ ወጥተው ቤተ ክርስቲያን ያቋቁማሉ።

ቤተ ክርስቲያን አንዲት እና የሁሉም ለሁሉም እንደሆነች ቢታወቅም እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በውጪው ሀገር ልዩ ልዩ ስም ወጥቶላት የእነ እከሌ ናት የእነ እከሌ አይደለችም የዚህ ዘር ናት የዚህ አይደለችም የውስጥ ናት የውጪ ናት በሚል ለባህርይዋ በማይስማማ ስም ስትጠራ ኖራለች። ይኽን ለዝከረ ነገር አነሳሁት እንጂ አሁን ሁሉም አልፏል፤ እግዚአብሔር ይመስገን ሁሉም ወደ አንድነት መጥቷል ቅዱስ ሲኖዶስ አንድ ሲሆን ያ ሁሉ መለያየት ጠፍቷል።

እኔ በአለሁበት የኦሃዮና አካባቢው ሀገረ ስብከት ከላይ እንደገለጥኩት ቀደም ሲል በሀገር ውስጥ ቅዱስ ሲኖዶስ እና በውጪው ቅዱስ ሲኖዶስ የሚመሩ አብያተ ክርስቲያናት ነበሩ። አሁን ቅዱስ ሲኖዶስ አንድ ሆኖ እርቅ ከተፈፀመ በኋላ እግዚአብሔር ይመስገን በአንድ ሀገረ ስብከት ሥር ሆነናል።

**መንፈሳዊ አገልግሎት በፍቅር ከአልሆነ ምንም ዋጋ እንደሌለው አምናለሁ፤ ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም መኖር እወዳለሁ፤ እኔ ዝቅ ብዬ ሌላው ከፍ ቢል ደስ ይለኛል። ተበድዬም እንኳን ስለፍቅር ይቅርታ እጠይቃለሁ ቅዱስ ጳውሎስ ፩ኛ ቆሮ ፰ ፥ ፲፫ “ነገር ግን በመብል ምክንያት ወንድሜ የሚሰናከል ከሆነ ወንድሜን እንዳላሰናክል ለዘለዓለም ሥጋን አልበላም።” እንዳለው . . .**

# “ከትናንቱ በመማር ዛሬ ላይ ጠንክረን ልንሠራ ይገባል”

**በእህተ ሚካኤል**



*መልአከ ገነት ቀሲስ መልአኩ ደሳለኝ*
*የምሥራቅ ሐረርጌ ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ*

***- መልአከ ገነት ቀሲስ መልአኩ ደሳለኝ***
***የምሥራቅ ሐረርጌ ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ***

## ክፍል አንድ

*የቤተ ክርስቲያን ጥቃትና መሰል ጉዳዮች ዙሪያ የሀገረ ስብከቱን ዋና ሥራ አስኪያጅ እንደሚከተለው አነጋግረናል ይከታተሉን፡፡*

***ስምዐ ጽድቅ፦*** አባታችን ይህን ቃለ መጠይቅ እንድናደርግ ስለፈቀዱልን በእግዚአብሔር ስም እናመሰግናለን፡፡ በቅድሚያ ሙሉ ስምዎትን ከየት እንደመጡና የአገልግሎት ድርሻዎትን ይግለፁልን

***መልአከ ገነት ቀሲስ መልአኩ ደሳለኝ፦*** እኔም እድሉን ስለሰጣችሁኝና እንድናገር ስለፈቀዳችሁልኝ በእግዚአብሔር ስም አመሰግናለሁ፡፡ መልአከ ገነት ቀሲስ መልአኩ ደሳለኝ እባላለሁ፡፡ የመጣሁት ከምሥራቅ ሐረርጌ ሀገረ ስብከት ሲሆን የአገልግሎት ድርሻዬም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የምሥራቅ ሐረርጌ ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ ነኝ፡፡

***ስምዐ ጽድቅ፦*** የክርስትና አገልግሎትና አጠቃላይ እንቅስቃሴው በሀገረ ስብከታችሁ ምን ይመስላል?

***መልአከ ገነት ቀሲስ መልአኩ፦*** የክርስትና አገልግሎትን በተመለከተ በምሥራቅ ሐረርጌ ሀገረ ስብከት ጽሕፈት ቤት ሥር ርእሰ ከተማው ሁለት ክልሎች ናቸው ያሉት፡፡ በርእሰ ከተማው የሀረሪ ክልል ሕዝባዊ መስተዳድር አለ፡፡ ከዚያ ውጪ ከአርባ አምስት በላይ የሚሆኑት አብያተ ክርስቲያናት የሚገኙት በምሥራቅ ኦሮሚያ ክልል ውስጥ ነው፡፡

እንደሚታወቀው ምሥራቁ ክፍል በአብዛኛው ኢአማንያን ወይም ሙስሊሙ እና ፕሮቴስታንቶች የሚበዙ ስለሆነ ያን ሁሉ ተጽዕኖ ተቋቁመን በተቻለ መጠን እንደ አቅማችን በስብከተ ወንጌሉም በሰንበት ትምህርት ቤቱም በመደራጀት በርእሰ ከተማውም ሆነ በገጠሩ ቤተ ክርስቲያን እየተንቀሳቀስን መንፈሳዊ አገልግሎት እንሰጣለን፡፡ ምእመኑ በክርስትናው እንዲጸና ፤በአብዛኛው በሙስሊሙ

*በሀገሪቱ ከመጣው ለውጥ ጋር ተከትሎ በተለያዩ ክልሎች ላይ ዘርፈ ብዙ ጥቃቶች ተፈጽመዋል፡፡ በሰው እና በንብረት ላይ ብዙ ጉዳት ደርሷል፤ ብዙዎች የተወለዱበትን፣ ያደጉበትን እና የኖሩበትን አካባቢ ለቀው ተሰደዋል፡፡ ብዙዎች ሕይወታቸውን አጥተዋል፣ ብዙ የነበራቸው ባንድ ጀንበር ንብረት አልባ ሁዋል፡፡ ለዚህ መሰሉ ጥቃት ከተጋለጡት ውስጥ ደግሞ አንደኛዋ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ናት፡፡ መንግሥት በተለዋወጠ እና ሀገሪቱ ላይ አንድ ነገር በተከሠተ ቍጥር ግንባር ቀደም የጥቃት ዒላማ የምትሆነው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ናት፡፡ ለዚህ ደግሞ ወደ ኋላ ሄዶ የመንግሥት ለውጥ ታሪካችንን ማየቱ በቂ ነው፡፡ ከሁለት ዓመት በፊት በነበረው የመንግሥት ለውጥ ጋር ተያይዞ ቤተ ክርስቲያን ብዙ መከራን አሳልፋለች፡፡ በእሳቱ ውስጥ ካለፉ ሀገረ ስብከቶች ውስጥ ደግሞ አንዱ የምሥራቅ ሀረርጌ ሀገረ ስብከት ነው፡፡ በወቅቱ የደረሰውን*

ኅብረተሰብ አካባቢ ያሉ ክርስቲያኖች እንዳይጠለፉ እና ወደ ሌላ እምነት እንዳይሄዱ ስብከተ ወንጌል እየሰጠን እንገኛለን።

***ስምዐ ጽድቅ፦*** የሀገረ ስብከቱን የቤተ ክርስቲያን እና የክርስትና ታሪክ ቢነገሩን?

መልአከ ገነት ቀሲስ መልአኩ ፦ የሀገረ ስብከቱ የክርስትና ታሪክ ሲነሣ በሐረር ከተማ ላይ ክርስትናው ጥንታዊ ነው። በቀደመው ዘመን አባቶቻችን እነ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ሲመሩት በነበረበት ጊዜ ከዋናው ከቤተ ክህነት ጀምሮ እስከ ታች ድረስ በመላው ሐረርጌ ተብሎ ነበር የሚጠራው። ሐረርጌ ብፁዕነታቸው ሲመሩት የነበረ ሀገረ ስብከት ነው። እነ ብፁዕ አቡነ አብርሃም ቀዳሚው፣ እነ ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል ቀዳማዊው የመሳሰሉ ብፁዓን አባቶች ጭምር በመላው ሐረርጌ እየተባለ ሲመሩት የነበረ ሀገረ ስብከት ነው።

ጥንታዊና አንጋፋ ሀገረ ስብከት ነበረ። በአሁን ሰዓት ግን እንደ አንጋፋነቱ፣ እንደ ትልቅነቱ እንደ ቀድሞው አይደለም። የዚህ ምክንያቱ ደግሞ መላው ሐረርጌ ተብሎ ባንድ ይጠራ የነበረው ሶማሊያ ሀገረ ስብከት፣ ድሬዳዋ ሀገረ ስብከት፣ምዕራብ ሐረርጌ ሀገረ ስብከት፣ ምራቅ ሐረርጌ ሀገረ ስብከት ተብሎ መከፋፈሉና በአብዛኛው አብያተ ክርስቲያናቱ የሚገኙት በገጠሩ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የገቢውም አቅም አነስተኛ እንዲሁም ምእመኑ በአብዛኛው በሙስሊሙ መካከል ያለ በመሆኑ ነው።

***ስምዐ ጽድቅ፦*** በአሁኑ ጊዜ ቤተ ክርስቲያኒቱን ለማጥፋት በተጀመረው ዘመቻ የጥፋት ዒላማ ከሆኑት ሀገረ ስብከቶች ውስጥ የእናንተ ሀገረ ስብከት አንዱ ነበር እስኪ ስለዚያ ይንገሩን

***መልአከ ገነት ቀሲስ መልአኩ፦*** በ፳፻፲፪ ዓ.ም ዘመነ ዮሐንስ በቤተ ክርስቲያን ላይ ትልቅ ጠባሳ ጥሎ አልፏል። ከጥቅምት የጀመረ የቤተ ክርስቲያን ጥቃት ሰኔ ወር መጨረሻ ላይ በአርቲስት ሀጫሉ ሞት ምክንያት በኛ ሀገረ ስብከት ከፍተኛ ጉዳት ደርሶአል። ከ፩፻፴፫ በላይ የሚሆኑ አባወራዎች ተፈናቅለው፤ ቤታቸው ተቃጥሎ ከ፮ ምእመናንን በላይ በመግደል፣ አስከሬናቸውን በመቆራረጥ እና መሬት ለመሬት በመጎተት ኢትዮጵያውያን ይፈጽሙታል የማይባል አፀያፊ ድርጊት የተፈጸመበት ቦታ ነው።

በተለይ ቦረዳ የምትባል ቦታ ላይ አቶ ዳመና የሚባሉ አባወራ ቤተ ክርስቲያንን የሚረዱ፤ ጠንካራ ክርስቲያን እና የቤተ ክርስቲያን ተቆርቋሪ ከነቤተ ሰቦቻቸው ነው ያለቁት፤ አሰቃቂ ግድያ ነው የተፈጸመባቸው።

***ስምዐ ጽድቅ፦*** ከሞት የተረፉትን እና ጉዳት የደረሰባቸውን ምእመናን ከማጽናናት አንፃር በሀገረ ስብከቱ ምን ምን ሥራ ተሠርቷል?

***መልአከ ገነት ቀሲስ መልአኩ፦*** እኔም ሆንኩ ሊቀ ጳጳሱ በዚያ ወቅት ነበር ለሀገረ ስብከቱ የተመደብነው። ሆኖም በጊዜው የነበረውን መከራ በመቋቋም በተቻለ መጠን ወደ ምእመናኑ በመሄድ በቃለ እግዚአብሔር ከማጽናናት እና ከማረጋጋት ባሻገር ከሀገረ ስብከቱ ወጪ በማድረግ የተለያዩ ቁሳቁሶችን ለመርዳት ሞክረናል። ከዚያም አልፎ ጊዜና ሰአት እያመቻቸን በመሄድ ብዙ አጽናንተናል። ነገር ግን የተወሰኑት ምእመናን ተደራርቦ የመጣውን መከራ በመሰቀቅ እና ተስፋ በመቁረጥ ትንሽ ገንዘብ ያለው ቤቱን መሠረቱን እየነቀለ እየሄደ ነው። የተወሰነው ደግሞ ለጊዜው በዚህ ሰዓት ተረጋግቶ ነው ያለው፤ እኛም ከጎናቸው አልተለየንም።

***ስምዐ ጽድቅ፦*** አካባቢውን እየለቀቀ የሚሄደው ክርስቲያን በቊጥር ይታወቃል ? ምን ያኽል ይሆናል?

***መልአከ ገነት ቀሲስ መልአኩ ፦*** እንግዲህ ይኼን ያህል ተፈናቅሎ ሄዶአል ለማለት ዳታው የለንም፤ ነገር ግን የተወሰኑ ምእመናን ወደ አዲስ አበባ፤ ወደ ናዝሬት እና ወደ ደብረ ዘይት እንደገቡ በተወሰነ ደረጃ ሰምተናል። በአብዛኛው ግን በዚህ በሐረር እና በዙሪያው ያሉ ምእመናን ኑሯቸው ከእጅ ወደ አፍ ነው፤ብዙም አቅም ያላቸው አይደሉም። በአሁኑ ሰዓት ያችኑ የፈራረሰች ቤት እየጠገኑ ለመኖር ተገደዋል።

***ስምዐ ጽድቅ፦*** በአጠቃላይ እንደ ምሥራቅ ሐረርጌ ሀገረ ስብከት የተጎዱዎች ቊጥር ምን ያህል ይሆናል? የተያዘ መረጃስ አለ ወይ? ሀገረ ስብከቱ ከሰጠው እርዳታ ውጪ በመንግሥት? በግለሰቦች? የተደረገ ነገር አለ?

**መልአከ ገነት ቀሲስ መልአኩ** ፦ በአሁን ሰዓት የተጎዱት እና በዝርዝር የያዝነው ዳታ ፩፻፵፫ አባወራዎች ናቸው:: የእያንዳንዱን የወደመበትን ንብረቱን ጨምሮ የተመዘገበ ነው:: ከእርዳታ ጋር ተያይዞ በዚህ በአዲስ አበባ የተቋቋመ እርዳታ የሚሰጥ ዐቢይ ኮሚቴ አለ:: ተጎጂዎችን በማቋቋም ሂደት ሥር ነቀል ለውጥ ለማምጣትና እስከመጨረሻው ለመደገፍ ፫ ቢሊየን ብር ተመድቧል:: በወቅቱ ግን የተሰበሰበው አርባ ሚሊየን ብር ለጠቅላላ ተጎጂዎች ማለትም በሌሎች ሀገረ ስብከቶችም ሲከፋፈል እንደ ምሥራቅ ሐረርጌ ሀገረ ስብከት የተሰጠው ፬ ሚሊየን ብር ነው:: ለምእመናኑ የተሰራው ገንዘብ መቀበያ ቡክም ለ፪፻፳፰ አባወራዎች ብቻ ነው የተሠራው:: የቀረው ምእመን ግን አልተሰራለትም:: በዚህ የተነሣ እኛ የተላከልንን ፪፻፳፰ ቡክ ለማከፋፈል ተቸግረናል:: ስለዚህ የተጎዳው ሳያገኝ ያልተጎዳው መለስተኛ ጉዳት የደረሰበት ቡክ ሲሰጠው እኛ ላይ ነው ችግሮች የሚፈጠሩት:: ስለዚህ ሁሉም ተሟልቶ አንዴ ቢሰጥ የሚል ሐሳብ አቅርበናል:: በእርግጥ በመንግሥት ደረጃም የተወሰነ እርዳታ እየደተረገላቸው ነው ቆርቆሮውንም ሚስማሩንም እንጨቱንም እየተሰጠ ወደየ ነበሩበት ለመመለስ ተችሎአል::

***ስምዐ ጽድቅ፦*** ጉዳት የደረሰባቸው ምእመናን ቁጥር የሚታወቅ ከሆነ ለምን ለ፪፻፳፰ አባወራዎች የሚሆን ቡክ ብቻ ተዘጋጀ? በጉዳዩ ላይ ተገናኝታችሁ ለመነጋገር አልቻላችሁም? ዐቢይ ኮሚቴው የሚያነሣው ምክንያትስ ይኖር ይሆን?

***መልአከ ገነት ቀሲስ መልአኩ፦*** በእርግጥ ምክንያታቸው አሳማኝ ነው:: ዐቢይ ኮሚቴው መጀመሪያ ላይ ገንዘቡን ሲያቀርቡ ለተጎጂዎች ለዘመን መለወጫ በዓል እንዲደርስ ተብሎ በችኮላ ነበር የተሠራው ፤ ከኛ ጋርም ግኙኝነት አልነበረም:: አርባ ሚሊየኑን በራሳቸው ወስነው ነው ለተጎጂዎች ለመከፋፈል የሞከሩት የምሥራቅ ሐረርጌንም በራሳቸው ያገኙትን ዳታ መሠረት አድርገው ነው ቡኩን የሠሩት:: እኛ የሰበሰብነውን የ፩፻፵፫ አባወራዎች መረጃ ሪፖርት የምናቀርበው በዋናው መሥሪያ ቤት በኩል ነው፤ እነሱ ብሩን ሲያከፋፍሉ መረጃውን ከኛ መውሰድ ነበረባቸው:: ሀገረ ስብከቱ ተጠይቆ መረጃ የሰጠው ነገር ያለ አይመስለኝም::

የ፴፱ኛውን ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ከጨረስን በኋላ የዐቢይ ኮሚቴው ም/ሰብሳቢ ሰብስበውን ነበር:: እኛም በሀገረ ስብከቱ ላይ የደረሰውን አስከፊ ችግር የሕዝቡን ከእጅ ወደ አፍ የሆነ የኑሮ ሁኔታ እንዲሁም ባቀረብነው ልክ አንዱ ከአንዱ ሳይለይ ለሁሉም ተጎጂዎች እኩል ቢሰጣቸው የሚል ሐሳብ አቅርበናል:: ከላይ እንደጠቀስኩት ዐቢይ ኮሚቴው አርባ ሚሊዮኑን ከአከፋፈሉ በኋላ መጠባበቂያ ብለው ያስቀመጡት ፳ ሚሊየን ብር ብቻ ነው:: ለኛም "የተሠራውን ወደ ፪፻፳፰ ቡክ ውሰዱና ለተራቡት ድረሱላቸው ከዚያ በኋላ ደግሞ በቀጣይ ስብሰባ ስላለን እናይላችኋለን" የሚል ምላሽ ነው የሰጡን:: በኛ በኩል በቂ መረጃ አቅርበናል አጋጣሚ ይህን ከተረዱ ቢያደርጉልን ደስታውን አልችልም:: ሆኖም ፪፻፳፰ ቡክ እንድንረከብ ግፊት እያደረጉ ነው ያሉት ያው መረከባችን አይቀርም::

***ስምዐ ጽድቅ፦*** አሁን በቊጥር ከተያዘው ፪፻፳፰ ውጪ ያሉትንና የከፋ ጉዳት ላይ ያሉ ምእመናንን ለመደገፍ በሀገረ ስብከት ደረጃ ያለው እንቅስቃሴ ምን ይመስላል?

***መልአከ ገነት ቀሲስ መልአኩ፦*** በዚህ ጉዳይ ዙሪያ በሀገረ ስብከቱ የሰላም ኮሚቴ ተብሎ የተቋቋመ ኮሚቴ ስላለ ዳታውን አስተካክለው ሠርተውታል:: ይኽ ኮሚቴ ዳታውን የሰበሰበው በእሳት ውስጥ አልፎ ነው:: እጅግ አስቸጋሪና ውስብስብ ነበረ:: በእኛ በኩል ችግር ያለባቸውን ለይተን ስም ዝርዝር አውጥተናል:: ይኽን ዝርዝር ስናዘጋጅ ለምሳሌ የስም ዝርዝር ችግሮች ገጥመውን ነበር:: የሰላም ኮሚቴው የስም ልውውጥም አድርገዋል ለምሳሌ በሞተም ሰው የተመዘገበውን በአለው ቤተሰብ ስም እንዲሆን ተደርጎ ተስተካክሎአል:: ያንን ግን ሄደን ለማስፈረም ቢያንስ ከሀገረ ስብከቱ ወደ አንዱ ችግር ወደ ደረሰበት ቦታ ለመሄድ ከ፲ ኪሎ ሜትር በላይ መጓዝ ያስፈልጋል:: ለዚያ የሚሆን እና ለተለያዩ ነገሮች ወጪ ጠይቂ ነበር:: ነገር ግን በሀገረ ስብከቱ እንዲሸፈን የሚል ሓሳብ ነው የቀረበው:: በእርጥ ሀገረ ስብከቱ ብዙ ነገር እየሸፈነ ይገኛል፤ብዙ ሥራም እየሠራ ነው፤ ይሸፍን ከተባለ እንሸፍናለን ፤ነገር ግን ቢያንስ የቀሩት ምእመናን ዳታ ተሞልቶ ቡክ እንዲሠራላቸው የሚል ጥያቄ አንስተንላቸዋል:: ዐቢይ ኮሚቴው ይኽን ጥያቄ አስመልክቶ የተጠየቀው ዳታ ወደፊት እንደሚሞላ ወይም ደግሞ ወደ CCRDA የተባለ ድርጅት(ወደ እዚያ ድርጅት የገባ ገንዘብ ስላለ) እንደሚያስተላልፉልን ነው የመለሱልን::

# ደጉ ሳምራዊ

በቀሲስ ዘክርስቶስ ፀጋዬ

የተወዳዳችሁ የእግዚአብሔር ልጆች! እንደምን ከርማችኋል? በእግዚአብሔር ቸርነት በሰላምና በጤና እንደቆያችሁን ተስፋ እናደርጋለን፤ ትምህርታችሁን በንቃት በመከታተል በመንፈሳዊም በሥጋዊም ዕውቀት ማደግ ይኖርባችኋልና በርቱ!

ልጆች! ዛሬ ይዘንላችሁ የቀረብነው ታሪክ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ አንድ ደግ ሳምራዊ ለአንድ ሕግ አዋቂ በምሳሌ ያስተማረውን ትምህርት ነው፤ መልካም ንባብ ይሁንላችሁ!

አንድ ቀን አንድ የሕግ ባለሙያ ጌታችን ኢየሱስን ሊፈትነው ቀርቦ "መምህር ሆይ የዘላለም ሕይወትን እንድወርስ ምን ልሥራ (ላድርግ)? ሲል ጠየቀው::"

ጌታችንም ለሕግ ዐዋቂው "በሕግ በመጽሐፍ የተጻፈውን አንተ እንዴት ታነባለህ?" ብሎ ጠየቀው፤ ሕግ ዐዋቂውም ለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህም፣ በፍጹም ኃይልህም፣ በፍጹም ሐሳብህም ውደድ፤ ባልንጀራህንም እንደራስህ ውደድ" በማለት መለሰለት::

ጌታችንም ለሕግ ዐዋቂው "እውነት መለስህ:: የዘላለም ሕይወትን ለማግኘት በሕይወትም ለመኖር ከፈለክ ጌታ አምላክህን በፍጹም ነፍስህ ውደድ፤ ባልንጀራህንም እንደራስህ አድርገህ ውደድ" አለው::

በዚህን ጊዜ ጌታችን ራሱን ከፍ አድርጎ ሌላውን ንቆ ጥያቄ ላቀረበው ሕግ ዐዋቂ ባልንጀራው ማን እንደሆነ እንዲረዳ እና ምን ማድረግ እንዳለበት የሚከተለውን ታሪክ በምሳሌ ሊነግረው እንዲህ በማለት ጀመረ::

በአንድ ወቅት አንድ ሰዉ ከኢየሩሳሌም ወደ ኢያሪኮ ተጓዘ:: በጉዞውም ሳለ በድንገት ወንበዴዎችና ሽፍቶች አገኙተውት መጥተዉ አስቆሙት:: ገንዘቡን ወሰዱ፤ ልብሱንም ገፈፉበት፤ ደብድበዉም፤ አቊስለው ሊሞት ሲቃረብ በመንገድ ላይ ጥለውት ሔዱ::

አንድ ካህን በዚያ መንገድ ሲሔድ ያን ተደብድቦ የወደቀውን ሰው ቀርቦም ቢያየው ተጎድቷል፤ ነገር ግን ሳይረዳዉ አልፎ ጥሎት ሔደ::

ከካህኑ ቀጥሎ ደግሞ አንድ ከሌዊ ወገን የሆነ ሰው በዚያ መንገድ ሲያልፍ በወንበዴዎች ተደብድቦ የወደቀዉን ሰዉ አገኘው እና አየዉ:: ነገር ግን እርሱም ሳይረዳዉ ዝም ብሎ በመንገድ ላይ እንዳየው እንደቀደመው ካህን ሌዋዊውም ገለል ብሎ አልፎት ሔደ::

ሦስተኛ አንድ ሳምራዊ በዚያች መንገድ ሲሄድ አገኘው፤ አይቶም አዘነለት፤ ወደ ቈሰለው ቀርቦ በቊስሉ ላይ እንዲያደርቅለት ወይን አደረገለት፤ እንዲያለሰልስለት ደግሞ ዘይት በቊስሉ ላይ አፈሰሰለት::



ደጉ ሳምራዊው የተደበደበውን ተጓዥ ሰው ቀርቦ ወዳለው እንግዳ ማረፊያ ስፍራም ከአስገባው በኋላ እየተንከባከበዉ፣ እያስታመመውና የሚፈልገውን እያደረገለት አብሮት በሰላም አደሩ::

በማግሥቱም ሁለት ዲናር አውጥቶ ለእንግዶች ማረፊያ ማደሪያ ወይም ማደሪያ ቤት ባለቤት ኃላፊ ለሆነው ሰው ሰጠዉ:: ከሰጠዉም በኋላ ይህን ሰው ተንከባከብልኝ "የምትከስረዉን ሁሉ እኔ ስመለስ እከፍልኀለው" ብሎ የተደበደበውን ሰው አደራ ሰጥቶት ወደ ሌላ ስፍራ ሔደ::

ልጆች! የጌታችንን ምሳሌውን እየተከታተላችሁ ነው አይደል? መልካም! ታዲያ ለዚህ ተደብድቦ በመንገድ ላይ ለወደቀዉ ሰዉ ባልንጀራዉ የሆነለት የትኛዉ ሰው ይመስላችኀኋል?

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የምሳሌውን ታሪክ የእግዚአብሔርን ሕግ ዐዋቂ ለሆነው ሰው ነግሮ ከጨረሰ በኋላ "ከእነዚህ ከሦስቱ ከካህኑ፣ ከሌዋዊዉ እና ከሳምራዊዉ በወንበዴዎች እጅ ለወደቀዉ ባልንጀራ የሆነዉ ማንኛዉም ይመስልሃል?" ሲል የሕግ ዐዋቂዉን ጥያቄ ጠየቀዉ::

እርሱም "ምሕረት ያደረገለት ነው" ብሎ መለሰለት::

ጌታችን ኢየሱስም ሕግ አዋቂ ለሆነው ሰው እንዲህ አለው "አንተም የዘላለምን ሕይወት ለመውረስ፣ በሕይወት ለመኖር ሕግን ማወቅ፣ ስለ ፈጣሪ ሕግ መናገር ፣ለሚጠየቁ ጥያቄዎች መልስን መስጠት ብቻ ሳይሆን፤ እንደ ሳምራዊዉ ሰዉ የአንተን እርዳታ ለሚፈልግ ማንኛውም ሰው መልካምን አድርግ" በማለት ነገረው::

"የወደቁ ሰዎችን እርዳ፣ ምሕረት አድርግ፣ ተንከባከብ:: ባልንጀርነት ማለት ምሕረት ማድረግ ማለት ነው:: ሒድ አንተም እንደ ሳምራዊው ምሕረት አድርግ በሕይወት ትኖራለህ" አለው:: (ሉቃ. ፲፥፳፭-፴፯)



ልጆች! ሳምራዊው እንደተመለከትነው በመንገድ ላይ ወድቆ ያገኘውን ቍስለኛ አንስቶ መልካም ነገር ስላደረገለት፣ ከወንበዴዎች እጅ ስላዳነው፣ ምሕረትም ቸርነትም ስለአደረገለት ደግ ሰው ይባላል::

ልጆች! እናንተም እንደ ደጉ ሳምራዊዉ ደግ ሁኑ፤ በጎም አድርጉ፤ የተቸገረ ማንኛዉንም ሰዉ መርዳት ይገባችኋል:: ሰዎች የእናንተን እርዳታ በሚፈልጉበት ጊዜ ደጉ ሳምራዊውን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በማሰብ በማንኛዉም ጊዜ ለሰዎች በጎ አድርጉ:: "እኔም እስከ ዓለም ፍጻሜ በዘመኑ ሁሉ ከእናንተ ጋር እኖራለሁ" ብሎም እንዳስተማረን ደግ ሰዎች ስትሆኑ ሰላማዊው ንጉሥ ኢየሱስ ክርስቶስ ከእናንተ ጋር ይሆናል!!! (ማቴ.፳፰፥፳)

ልጆች! ለዛሬ በዚህ ላይ ይብቃን፤ በሚቀጥለው ትምህርታችን እስክንገናኝ ደኅና ሰንብቱ!

*እግዚአብሔር ይባርካችሁ!*

*ምንጭ፦ "ደጉ ሳምራዊ" ከ፯-፲፩ ዓመት ላሉ ልጆች ከተዘጋጀ የሕፃናት መጽሐፍ፤ ፳፻፲ ዓ.ም የተወሰደ::*

# ‹‹አክቲቪስቶቹ›› ካህናት

ኪኑኪሩ ከአዲስ አበባ

ይሄ ማኅበራዊ ሚዲያ የሚባል ጉድ የስንቱን ጠባይ፣ ፍላጎትና ገበና ገለጠው?! ሰው እንዴት ከልብሱ አልፎ ገላውን፣ ከገላው አልፎ ነፍሱን አራቁቶ ያሳያል?! ጎበዞች ሆይ! ማኅበራዊ ሚዲያ ሰዎች ክብራቸው በነውራቸው እንዲሆን የመፍቀድ ልምምዳቸው ማሳያ አደባባይ እየሆነ መምጣቱን እንደ እኔ አስተውላችሁ ይሆን! ሞራል፣ ሥነ ምግባር፣ ሕግ በይፋ ሲሰባበሩ የሚታይብት የፍልሚያ ሜዳ አይታያችሁም?

ማኅበራዊ ሚዲያ የሚያሳየን የሁሉንም ገመና ሆኗል፤ የሴቱን ብቻ አይደለም፤ የወንዱንም ነው፤ የደቂቁን ብቻ አይደለም የልሂቁንም ነው፤ የኢ-አማኒውን ብቻ አይደለም የምእመኑንም ነው፤ ያልተማረውን ብቻ አይደለም የተማረውንም ነው። እረ ስንቱን!

በየቤቱ ቤተሰብ የቻለው ጉድ አሁን የሁሉም ሕዝብ ሆኖ ማኅበረሰብ እንዲሸከመው ሆኗል። አሁን በቤተሰብህ ብቻ ሳይሆን በጎረቤትህ አመል ትታወካለህ።

ይሄ ጉድ ሄዶ ሄዶ ከቤተክርስቲያን ቄሱን፣ ዲያቆኑን፤ ከገዳም መነኮሳቱን መንካቱ ደግሞ ‹‹የቤቱው ጉድ›› እንድል አስገድዶኛል። የዛሬም ትዝብቴ ከብዙ ኃላፊነት ተሰምቷቸው የእግዚአብሔርን አደራ ጠብቀው ቀን ከሌት ስለሕዝባቸው በመንፈስ ሲጋደሉ ከሚኖሩ ካህናት ተርታ ወጥተው ‹‹አክቲቪስት›› ስለሆኑ ጥቂት ካህናት ነው። ሌት ከቀን በማኅበራዊ ሚዲያ ዕድሎቻቸው መልካሙን ዜና ከሚያወሩና ከሚነግሩን ብርቱ አገልጋይ መምህራን ይልቅ ጥቂት ‹‹አክቲቪስት›› ስለተባሉ አገልጋዮች ነው።

መቼም ካህናት እና የእግዚአብሔር አገልጋዮች እናንተ ‹‹የምድር ጨው ናችሁ›› ብሎ አልጫውን ዓለም እንዲያጣፍጡ የታዘዙ ሆነው ሳለ፤ እነዚህ ጥቂት ‹‹አክቲቪስት›› ካህናት አልጫነቱ እየባሰበት ከመጣው ዓለም ጋር አብረው የጨውነት ክብርና መዓርጋቸውን ማውለቃቸውን ያየንበት አንዱ መድረክ ይሄው የማኅበራዊ ሚዲያ ከሆነ ሰነባበተ። ‹‹ጨው አልጫ ቢሆን በምን ይጣፍጣል?›› ይልሃል ይሄው ነው።

ካህናት ‹‹የእግዚአብሔር ዓይኖች›› ናቸው፤ ሰውን ሁሉ እንደ ፈጣሪው በእኩልነት የሚያዩ የእርሱም እንደራሴ ሆነው የሚያገለግሉ ናቸው፤ አንዱን ሰው ከአንዱ አስበልጠው ሲያሞግሱ ሲያወድሱ፣ ሲከሱ ሲወቅሱ ያየናቸው ‹‹አክቲቪስት›› ካህናት ግን ከጊዜ ወደ ጊዜ ቊጥራቸው እየጨመረ ነው። በየኪሱ ዘውድ ይዞ ከሚዞረው እገሌ ወይም እገሌ ከሚባለው የፖለቲካ ወገን ጋር እየወገኑ አንዱን ሲያነሡ፣ ሌላውን ሲከስክሱ አይተናል። አንዱን ቋንቋ ተናጋሪ ከሌላው ቋንቋ ተናጋሪ ለይተው ሲክቡ ሌላውን ሲያዋክቡ አይተናል። የአንዱን ባህልና ታሪክ ከሌላው ባህልና ታሪክ እያበላለጡ ሲያራክሱ ወይም ሲቀድሱ አይተናል። የእነዚህ ‹‹አክቲቪስቶች›› ዓዕይንተ እግዚአብሔርነት ወዴት አለ! ‹‹እግዚአብሔር ለሰው ፊት አያዳላምና።›› /ሮሜ 2፥11/ እጅግ አስገራሚው ነገር እነዚህ ወገኖች የእኛ አይደሉም እንዳንላቸው የሃይማኖት ካባ አጥልቀዋል፤ ነገር ግን መሸ፣ ነጋ ብሎ ቤተክርስቲያን የምትናፍቀውን ምእመን የእነሱ የማኅበራዊ ሚዲያ ጨኸት እንዲናፍቀው ይሠራሉ። ‹‹አክትቪስት›› ካህናቱ ከምእመኑ ፊት ተደንቅረው ቤተ መቅደሱን እንዳያይ፣ ምዕመኑን ከሃይማኖቱ አፋተው የዩቲዩብ የገንዘብ ምንጭ አድርገውታል፤ ሐዋርያው እንዳለ ለመንጋው የማይራሩ ጨካኞች እየሆኑብን ነው።

አገልጋይና የቤተክርስቲያን ባለውለታ ተደርገው ሲታሰቡ ቆይተው ያገኙትን አንቱታቸውን፣ ታዋቂነታቸውን ተጠቅመው ሕዝበ ክርስቲያኑን ወደ ገደል ስለሚገፉ ዓለምን ከነትብታቧ ጎትተው ወደ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ስላስገቡ ስለእነዚህ ወገኖች ወይም ‹‹አክቲቪስት›› ካህናት ምን እንበል?

የእግዚአብርሔርን ቃል እንደሚሸቃቅጡት ተብሎ እንደተጻፈ ወንጌልን ሊሰማቸው ልቡን ሰጥቶ ጆሮውን ከፍቶ ለሚያዳምጣቸው የዋህ ምእመን ፖለቲካውን ከወንጌል መሳ ለመሳ አድርጎ በማቅረብ የቤተ ክርስያንን ፍቅር የተሞላበት የአገልግሎት መንገድ በጥላቻና መለያየት እየተኩ ስላሉ አክትቪስት ካህናትስ ምን እንበል? ግራ ገባን እኮ!

ካህናት ለቤተክርስቲያን አንድነት ሲሉ ራሳቸውን ያስጨንቃሉ እንጂ ቤተክርስቲያንን ለመከፋፈል እንዴት ይጨነቃሉ፤ በሚለጥፉት ፎቶ፣በሚጽፉት ጽሑፍ፣ በሚናገሩት ቃል፣ በሚሰጡት አስተያየት የአንዱን ቍስል ሲታመሙለት በአንዱ ቍስል ደግሞ እንጨት ሲሰዱበት የሚያዩስ አሕዛብ ስለቤተከክርስቲያን ምን ይላሉ? ‹‹በእናንተ ሰበብ የእግዚአብሔር ስም በአሕዛብ መካከል ይሰደባልና ተብሎ እንደ ተጻፈ።›› /ሮሜ ፪፥፳፬/።

ስለሰው ሁሉ መከራ ማልቀስ የሚገባቸው እነዚህ ካህናት በማኅበራዊ ሚዲያዎች በሚናገሩት ቃልና ጽሑፍ የሚያስለቅሱት እንዳለ እንዴት አላስተዋሉም። የሚደግፉት የፖለቲካ ቡድን ጫፉ ከሚነካ ቤተክርስቲያን ብትንካካ የማይገዳቸው መሆናቸውን በሚያነክስ ቃልና ጽሑፎቻቸው ውስጥ ብዙ ታዝበናል። የሚችሉትን መክረው፣ የማይችሉትን ለእግዚአብሔር በጸሎት አሳስበው መልካሙ እንዲመጣ ማድረግ ሲገባቸው ‹‹እገሌ ይታሰር፣ እገሌ ይሰቀል፣ እገሌ ይውረድ፣ እገሌ ይውጣ፣ እገሌ ይምጣ፣›› ሲሉ የሚውሉ እነዚህ ‹‹አክቲቪስቶች›› እርስ በእርስ እንኳን በሐሳብ አንድ ሆነው አለመገኘታቸው እንደውም በተቃራኒ ጎራ ሆነው መፋለማቸው ምን ያህል ሐሳባቸው ምድራዊ እንደሆ ለትዝብት አይዳረጉም ትላላችሁ!

የእነዚህ ‹‹አክቲቪስቶች›› ክህነታቸው ከአንድ ቤት ከአንድ መንፈስ ይቀዳል፤ የተሰጣቸውን ጸጋና ኃላፊነት ግን ስለረሱ አንድ ሐሳብ አንድ ልብ የላቸውም፤ አንዱ ከሰሜን ሆኖ የደቡቡን ያሳምማል፤ አንዱ ከምሥራቁ ሆኖ የምዕራቡን ያቃልላል። ያነሣሣል፤ ያጋግላል፤ ያጋድላል። ፍቅርን ከሚያመነጭ ከክርስቶስ የክህነት ጸጋ ጥላቻ እንዴት መነጨ! አንድነትን ከሚያመንጭ ከክርስቶስ የክህነት ጸጋ መለያየት እንዴት መነጨ? ‹‹እኛስ የክርስቶስ ልብ አለን›› ብለው ሰብከው ሲያበቁ፤ ዓለምን በሚያዩበት መነጽር ግን እንዴት በውስጠቻው ያለውን የክርስቶስን ልብ ከፋፈሉት? ‹‹ ክርስቶስ ተከፍሎአልን? ›› /፩ኛ ቆሮ ፩፥ ፲፫/

እውነትን አይተው እንደሚፈርዱ፣ ስለእውነትና ስለፍትህ እንደሚቆሙ እያስመሰሉ የሥጋ መሻታቸውን በፌስ ቡክ ገጾቻቸው፣ በቴሌግራም ቻናላቸው ሲለቁ ማየት እጅግ ያሳዝናል። ሰዎችን ማጣላታችን አንድ በደል ነው፤ መታረቅ እስከማይችሉበት ጥግ ወስዶ፣ በክፉ ሐሳብ ግራና ቀኝ ሆኖ መረጫጨት ግን የበለጠ አሳዛኝ ነው። ካህናት እስከ ደም ድረስ ለማስታረቅ ይጋደላሉ እንጂ እንደ እነዚህ ጥቂት ብልጣብልጦች ለማጣላት አይተጉም። ካህናት የሰውን ክፉ መንፈስ ያሳድዳሉ እንጂ በእነርሱ ምክንያት ሰው ከቤተክርስቲን እንዲሰደድ ማድረግ ሌላ ነገር ነው። ይህ በእውነት ምን እንለዋለን? ጀግንነት ነውን? ሰማዕትነት ነውን? ፍርድ አዋቂነት ነውን? የሰላም ሰባኪነት ነውን? በእነዚህ ጥቂት ‹‹አክቲቪስት›› ካህናት ምክንያትስ የሚጎድፈው የካህናት መልክ ታስቧቸው ያውቅ ይሆን? እነዚህ ጨለምተኛ ካህናትስ ተስፋን ከምትሰብክ ቤተክርስያን ማሳያ ሆነው መገለጣቸው ለምን ያህል ጊዜ ዕዳ ሆኖ ያቆይብን ይሆን? እርሱ ይወቀው።

እና ምን እናድርግ ለሚሉንም ያለን የመፍትሔ ሐሳብ እንደ እውነተኛ ካህን ሁሉን እናገልግል፤ በማኅበራዊ ሚዲያ መጠቀምን መሸሽ ሳይሆን ለሁሉ የሚጠቅም ሁሉን የሚገዛ ሐሳቦችን እናንሸራሽር፤ የሚዲያ ዕድላችንን ለሁሉ መድኃኒት የሆነውን ቃለ እግዚአብሔር ለሰው ሁሉ በየቋንቋው እናድርስ። ከሥጋ ለባሽ ሰው ይልቅ መንፈስ ከሆነው ሰይጣን ሥራና ሐሳብ ጋር እንዋጋ።

መነሻዬ እነርሱን መጥላት አይደለም፤ ምኞቴ የእነርሱ ጥፋት አይደለም፤ ሐሳቤ ለእነዚህ አክቲቪስት ካህናት ‹‹ነገርን ሁሉ በልክ አድርግ፥ የወንጌል ሰባኪነትን ሥራ አድርግ፥ አገልግሎትህን ፈጽም።›› /፪ኛ ጢሞ ፬፥ ፭/፤ ዳግመኛም ‹‹የጌታም ባሪያ ለሰው ሁሉ ገር ለማስተማርም የሚበቃ ለትዕግሥትም የሚጸና ሊሆን እንጂ ሊጣላ አይገባውም።›› /፪ኛ ጢሞ ፪፥ ፳፬/ ያለውን የሐዋርያውን ቃል ማስታወስ ብቻ ነው። ሰላሙን ይስጠን።

# ''ከልክ ያለፈ ፍርሀት ሕይወቴን ተፈታተናት''

*የተወደዳችሁ የስምዐ ጽድቅ አዘጋጆች እንደምን አላችሁ? ከሰላምታዬ በመቀጠል የማካፍላችሁ ችግሬ እንዲህ ነው፦ ስሜ ክንፈ ሚካኤል ይባላል፤ ዕድሜዬ ሠላሳዎቹ መጀመሪያ ላይ ነው:: ‹‹ከልክ ያለፈ ፍርሃት ሕይወቴን አስቸጋሪ እያደረገብኝ ነው››:: ምንም እንኳን ንስሓ አስፈላጊ እንደሆነ ባውቅም ወደ አባቶች ቀርቤ ኃጢአቴን መናዘዝ እየፈለኩ ግን በፍራቻዬ የተነሣ አልቻልኩም:: ከሰዎች ጋር አብሬ ጊዜ ለማሳለፍም እፈራለሁ፤ ከዚህ በተጨማሪም ጋብቻን ለመመሥረት ሀሳቡና ፍላጎቱ ቢኖረኝም ግን ሴቶችን መቅረብ እፈራለሁ:: በመሆኑም ፍርሃት በሥጋዊና መንፈሳዊ ሕይወቴ ላይ ተጽእኖ አሳድሮብኛል:: ከዚህ ችግር ነጻ ለመውጣት ብጸልይም መፍትሔ አላገኘሁም፤ አሁን አሁን ጭንቀት እየተሰማኝ ነው፤ ታዲያ ከዚህ ችግር እንዴት መውጣት እችላለሁ::*

*ውድ ወንድማችን ክንፈ ሚካኤል በቅድሚያ ታሪክህን ስላካፈልከን እናመሰግናለን፤ ይህ ዓይነቱ ታሪክ የሌሎች እኅቶች እንዲሁም ወንድሞች ሊሆን ስለሚችል እና አስተማሪ በመሆኑ ለዚህ ዝግጅት እንዲስማማ አድርገን አቅርበነዋል፤ መልካም ንባብ::*

ፍርሃት ስሜት እንደመሆኑ መጠን ሰው ሆኖ የፍርሃት ስሜት የማይሰማው የለም:: ነገር ግን ከልክ ያለፈ ፍርሃት የሰውን ሕይወት አስቸጋሪና ፈታኝ ያደርገዋል:: ስለዚህ ከልክ ያለፈ የፍርሃት ስሜት የሚሰማን ከሆነ በሕይወታችን ላይ ከሚያስከተለው ተጽዕኖ ነጻ ለውጣት መፍትሔ መፈለግ ያስፈልጋል::

የፍርሃት ስሜት ሁሉ በራሱ መጥፎ አይደለም:: አንጻራዊ መጠነኛ ፍርሃት ጠቃሚ ሊሆን ይችላል:: ፍርሃት ጠቃሚ ነው ሲባል ሰው ራሱን በሕይወቱ ሊያጋጥሙት ከሚችሉ አሉታዊ ሁኔታዎች ለመከላከል ዝግጅት ለማድረግ የሚያስችለው ተፈጥሮዊ ስሜት ስለሆነ ነው:: ስለዚህ የፍርሀት ስሜት የራሱ ጥቅም አለው የሚባለው ሰው በአካባቢው ሊያጋጥሙት ከሚችሉ ውጫዊ እና ውስጣዊ ችግሮች ራስን ለመጠበቅ የሚያስችል ስለሆነ ነው:: ከዚህ በተለየ ከልክ ያለፈ ፍርሃት ግን ሰው ሊያጋጥመኝ ይችላል ብሎ ለሚያስበው አሉታዊ ሁኔታ ራሱን እንዳያዘጋጅ ያደርጋለል:: በሰው ሕይወት ላይ አሉታዊ የስሜት ጫና በመፍጠር ጉዳት ያስከትላል:: ከዚህ በተቃራኒው ከልክ ያለፈ ፍርሃት ማጣት ደግሞ ሰው ሊመጣብኝ ይችላል ብሎ ለሚገምተው አሉታዊ ሁኔታ ራሱን እንዳያዘጋጅ ስለሚደርገው በሰው ላይ የከፋ አደጋ ሊያስከትል ይችላል:: የባለታሪካችንን ሕይወት ስንመለከት ከልክ ያለፈ ፍርሃት ሕይወቱን ተቆጣጥሮት እንመለከታለን:: ገና ለገና ኃጢአቴን ብናዘዝ ምን ይሉኛል፤ ከሰዎች ጋር ብቀራረብ መዝነውኝ ብቀልስ፤ልቤ የፈቀዳትን ሴት ለጓደኝነት ጠይቄያት እሺ ባትለኝስ በሚሉ የፍርሃት ስሜቶች መፈጸም ያለበትን ተገቢ ነገር እንዳይፈጽም እያደረገው ነው:: ስለዚህ የትኛው ፍርሃት ተገቢ እንደሆነ የትኛው ፍርሃት ተገቢ እንዳልሆነ መለየቱ ጠቃሚ ነው::

## ተገቢ ያልሆነ ፍርሃት

አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያትን ‹‹ሥጋችሁንም የሚገድሉትን አትፍሩአቸው፤ ነፍሳችሁን ግን ሊገዱሉአት አይችሉም፤ ነገር ግን ነፍስንም ሥጋንም አንድ አድርጎ በገሃነም ማጥፋት የሚቻለውን እርሱን ፍሩት›› ብሎአቸዋል (ማቴ፲፥፳፰) ። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን የተናገረው ማንን መፍራት እንዳለብን እንድንረዳ ነው:: አንዳንዶቻችን ግን ሰው እንዲህ ሊለኝ ይችላል ወይም እንዲህ ሊከሰት ይችላል ብለን ባልተጨበጠ ነገር እንፈራለን:: በእርግጥ እኛ ሙሉ በሙሉ ከፍርሀት ስሜት ነፃ ለመሆን እንቸገር ይሆናል ነገር ግን ከልክ ያለፈ ፍርሃት ሊሰማን ግን አይገባም::

ብዙ ጊዜ በሥጋ የሆነ ፍርሃት ይሰማናል፤ ይህ ፍርሃት ሰው ሕገ እግዚአብሔርን መተላለፉን ተከትሎ የመጣ እንጂ በጥንተ ተፈጥሮ የነበረ እንዳልሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል:: ነገር ግን ከዚህ አይነቱ ያልተገባ ፍርሃት ነጻ

መውጣት እንደሚቻል ልናምን ያስፈልጋል፡፡ ምክንያቱም እኛ ክርስቶስ በሞቱ የዳንን፤ የሞተልንን አምላክ በእምነት የምናውቅ ክርስቲያኖች ነን ‹‹እመን ብቻ እንጂ አትፍራ›› (ማር. ፭፥፴፮) እንደተባለ ጽኑ እምነት ያለው ሰው ያልተገባ ፍርሃት አይገዛውም፡፡

አስቀድሞ ሰዎች እንዲህና እንዲያ ይሉናል፤ እንዲህና እንዲያ ያደርጉናል በሚል ያልተጨበጠ የፍርሃት ስሜት ውስጥ ልንኖር አይገባም፡፡ እኛ በቻልነው መጠን ምንን እና ማንን መፈራት እንዳለብን ተረድተን ልንኖር ያስፈልጋል፡፡ ብዙ ጊዜ የፍራቻችን መነሻ ምክንቶች በአስተዳደጋችን ወቅት በሚያጋጥም ጉድለት፤ ከአእምሮ ጤና ጋር የተያያዘ፤ከመንፈሳዊ ሕይወት ጉድለት የተነሳ ሊሆን ይችላል፡፡ ባለታሪካችን ፍርሃትህ መነሻ የቱም ይሁን ካህናት አባቶችን፤ሴት እኅቶቻችንንና ሌሎች ሰዎችን መፍራትህ ተገቢ ቢሆንም ሰዎችን ማክበር እንጂ መፍራት አይገባም፡፡ ከሁሉ በላይ ተገቢው ፍርሃት የቱ እንደሆነ ልታውቅ ልትረዳ ይገባል፡፡

## ተገቢ የሆነ ፍርሃት

ፍርሃታችን ተገቢ የሚሆነው ከሰው ይልቅ እግዚአብሔርን ስንፈራ ነው፡፡ ቅዱስ ዳዊት ‹‹ለእግዚአብሔር በፍርሃት ተገዙ፥ በረዓድም ደስ ይበላችሁ›› (መዝ. ፪፥፲፩) ብሎ የተናገረው ለእግዚአብሔር በፍርሃት በመገዛታችን ተገቢ ና ዋጋ ያለው በመሆኑና ደስ ሳይሰኙ መገዛት ዋጋ ስለማያስጥ ደስ ልንሰኝ ይገባል ሲለን ነው፡፡ ነቢዩ ይህንን የተናገረው ተገቢ የሆነው እግዚአብሔርን መፍራት ክፉ ከመስራት እንድንርቅ ፤ መልካም ለመስራት እንድንበረታ ስለሚያደርገን ነው፡፡

እግዚአብሔርን መፍራት ተገቢና ጥበብም መሆኑን ሰሎሞን ሲናገር ‹‹ነገር ግን እግዚአብሔርን መፍራት የጥበብ ሁሉ መጀመሪያ ናት›› (ምሳ ፩፥፯) ይላል ፡፡እግዚአብሔርን የምናከብረው አክብሮት፣ የምንፈራው ፍርሃት በፍቅር ላይ የተመሠረተ ነው እንጂ እንደ ምድራዊ ንጉሥ ያጠፋኛል፤ ይቀጣኛልም ብለን እንዳልሆነ ልንገነዘብ ይገባል፡፡ እንዲሁም ደግሞ ፍጹም ፍቅር ፍርሃትን አውጥቶ ይጥላል እንጂ በፍቅር ፍርሃት የለም ፍርሃት ቅጣት አለውና የሚፈራም ሰው ፍቅሩ ፍጹም አይደለም ይላል (፩ ዮሐ. ፬፥፲፰፣ ምሳ. ፩፥፯) ፡፡ ባለታሪካችን ኃጢአቱን ለመናገር ፍርሃት አለበት ይህ ደግሞ ተገቢ ፍርሃት አይደለም፡፡ ‹‹ኃጢአቱን የሚሰውር አይለማም የሚናዘዝባትና የሚተዋት ግን ምሕረትን ያገኛል፡፡ ›› ምሳ ፳፰፥፲፫

## ያልተገባ ፍርሃትን እንዴት ማስወገድ ይቻላል?

አንድ ሰው የሚሰማውን ያልተገባ የፍርሃት ስሜት በግልጽ ከተረዳ እና የዚያ ስሜት መንስኤው ምን እንደሆነ መረዳት ሲችል ችግሩን ለማስወገድ እምብዛም አይቸገርም፡፡ ውድ ወንድማችን ከጽሑፍህ መረዳት እንደቻልነው ከልክ ያለፈ የፍርሃት ስሜት እንዳለብህና ይህ የፍርሃት ስሜት ያስከተለብህ ችግሮች መኖራቸውን ነው፡፡ በእርግጥ የሚሰማህ ተገቢ ያልሆነ የፍርሃት ስሜት ነው፡፡ ከዚህ የፍርሃት ስሜት ለመውጣት ደግሞ ችግሩ እንዳለብህ ማመንህ መልካም ጎን ሲሆን ከዚህ ችግር መውጣት እንደምትችል፣ ለዚህም የእግዚአብሔር ተራዳኢነት በማመን እርሱን ተስፋ ልታደርግ ይገባል፡፡

ውድ ወንድማችን ከላይ ለማንሳት እንደሞከርነው ሰው እግዚአብሔርን ከማፍቀር የተነሳ እንደ አባትነቱ ሊፈራው ይገባል፡፡ የዚህ ዓይነቱ ፍርሃት ደግሞ ተገቢ የሆነው ፍርሃት ነው፡፡ ነገር ግን ኃጢአትህን ለመናዘዝ፤ ራስህን ለካህን ለማሳየት መፍራትህ ተገቢ አይደለም፡፡ በመጀመሪያ መረዳት ያለብህ ኃጢአት ሰውን ከእግዚአብሔር የሚለይ ትልቅ ግድግዳ ነው፡፡ በመሆኑም ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ዳግም ኅብረት እንዲኖረው በንስሓ ሊመለስ ይገባል፡፡

ወንድማችን ክንፈ ሚካኤል አንተ በንስሓ መመለስ ተገቢ መሆኑን አውቀህ ኃጢአትን ለመናዘዝ ግን መፍራትህ የእግዚአብሔርን ቸርነት ርኅራኄ አለመረዳት ነው፡፡ ለዚህ ነው ሐዋርያው ‹‹አባ አባት ብለን የምንጮህበትን የልጅነት መንፈስ ተቀበላችሁ እንጂ እንደገና ለፍርሃት የባርነትን መንፈስ አልተቀበላችሁምና›› (ሮሜ ፰፥፲፭) በማለት የእግዚአብሔርን አባታዊ ፍቅሩን እንድንረዳ የሚስገነዝበን፡፡ አንተም የእግዚአብሔር ፍርዱን ብቻ ሳይሆን አባታዊ ፍቅሩን ዘወትር ልታስብ ያስፈልጋል፡፡ እርሱ የሰጠን እኛም የተቀበልነው መንፈስ ያልተገባ ፍርሃት እንድንፈራ

የሚያደርገን አይደለም ‹‹እግዚአብሔር የኃይልና የንጽሕና፥ የፍቅርና የጥበብ መንፈስን እንጂ የፍርሃት መንፈስን አልሰጠንምና፡፡›› ( ፪ኛ ጢሞ. ፩፥፯) ስለዚህ እግዚአብሔርን ከፍቅር በመነጨ ፍርሃት ልትቀርበው እንጂ ገና ነገና በኃጢአትህ አፍረህና ኃጢአትን መናዘዝ እስከመፍራት በሚያደርስ ከልክ ባለፈ ፍርሃት ውስጥ መኖር የለብህም፡፡

አሁን ካለህበት ሁኔታ ለመውጣት የአንተ ጥረት እና መልካም ሐሳብ እንዳለ ሆኖ ሐሳብህ ወደ ተግባር የሚለወጥበትን መንገድ ማመቻቸት አለብህ፡፡ ለዚህም የንስሓ አባት ከሌለህ አንድትይዝ ካለህ ደግሞ ቀርበህ የሚሰማህን የፍርሃት ስሜት ለንስሐ አባትህ በመንገር ፣ ምክር መቀበል ፣ መጸም እና መጸለይ በሕይወትህ ላይ ትልቅ ለውጥ ያመጣል፡፡ ከንስሓ አባትህ ተከታታይ የሆነ የምክር አገልግሎት ብታገኝ ካለህበት ችግር ለማገገም ብሎም ዘለቄታዊ መፍትሔ ልታገኝ ትችላለህ፡፡

ሌላው ባልተገባ ፍርሃት ምክንያት ልብህ የፈቀዳትን ሴት ቀርበህ የልብህን ሐሳብ መናገር እንዳልቻልህ ገልጸህልናል፡፡ ቅድመ ጋብቻ ጓደኝነት ለመጀመር ስታስብ ጋብቻን ዓላማ አድርገህ መጀመር አለብህ፡፡ ትውውቅ፣የጓደኝነት ጥያቄ ማቅረብ ፣መጠናናት፣መተጫጨት በቅድመ ጋብቻ ውስጥ ያሉ ሂደቶች ናቸው፡፡ አንተ ገና በትውውቅ ደረጃ ላይ የተቸገርህ ስትሆን ለዚህም አስቀድመህ የሥነ-ልቡና ዝግጅት ማድረግ ይጠበቅብሀል፡፡ አንተ ውስጥ የፍርሃት ስሜት እንዲፈጠር ከሚያደርጉ ሐሳቦች መካከል ምናልባት ጠይቄ እሺ.ታዋን ባላገኝ፤ ጓደኛ ቢኖራትስ፣እሷ በወንድምነት ብቻ ምታስበኝ ከነበረስ ወዘተ ሊሆን ይችላል፡፡ ፍቃዷን ስትጠይቅ መልሷ አሺታ ሊሆንም ላይሆንም እንደሚችል ራስህን በሥነ ልቡና ልታዘጋጅ ይገባል፡፡ስለዚህ ፍቃዷን ማወቅ የምትችለው ደግሞ ስትጠይቅ ብቻ ነው፡፡ ከአንተ የሚጠበቀው በጨዋ ደንብ ጥያቄህን ማቅረብ ብቻ ነው፤ ቀሪው የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው፡፡ አንድ ጊዜ አልሆነም ማለት ደግሞ ሁልጊዜ አይሆንም ማለት አይደለም፡፡ ልብህ የፈቀዳት ሴት ስታገኝ ከክርስትና መንገድህ የማታሰናክልህ እስከሆነች ድረስ ጥያቄ ለማቅረብ ልትፈራ አይገባም፡፡ ‹‹እኔ ከአንተ ጋር ነኝና አትፍራ፤ እኔ አምላክህ ነኝና አትደንግጥ፤ አበረታሃለሁ፥ እረዳሀማለሁ፤ በጽድቄም ቀኝ ደግፌ እይዝሃለሁ፡፡›› (ኢሳ. ፵፩፥፲) ሐሳብህ በጎ እስከሆነ ድረስ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር እንደሆነ ካመንህ ካልተገባ የፍርሃት ስሜት ሊሰማህ አይገባም፡፡ መፍራት አንድም የእምነት ጉድለት ነው፤ ስለዚህ በእግዚአብሔር ላይ ያለህ እምነት ሊያድግ ይገባል ‹‹እግዚአብሔር ያበራልኛል፤ ያድነኛል፤ ምን ያስፈራኛል? እግዚአብሔር የሕይወቴ መታመኛዋ ነው፤ ምን ያስደነግጠኛል? … በመከራዬ ቀን በድንኳኑ ሸሸጎኛልና፥ በድንኳኑም መሸሸጊያ ሰውሮኛልና፥ በዓለት ላይ ከፍ ከፍ አድርጎኛልና፡፡›› (መዝ. ፳፮፥፩-፫) ብለህ ዘወትር ልትጸልይ ይገባል፡፡

ሌላው ባለታሪካችን ያልተገባ የፍርሃት ስሜት ማኅበራዊ ሕይወትህ ላይ ተጽዕኖ አሳድሮብሀል፡፡ ክርስትና በተግባር ከሚገለጥባቸው ዐውዶች አንዱ ማኅበራዊ ኑሮ ነው፡፡ ምንም እንኳን ከሰዎች ጋር አብሮ ለመሆን የፍርሃት ስሜት ቢሰማህም ሰውን መፍራት ተገቢ እንዳልሆነ ተረድተህ ዘወትር ‹‹እኔ ግን በአንተም ታመንሁ፡፡ በእግዚአብሔር ቃሉን አከብራለሁ፤ በእግዚአብሔር ታመንሁ፥ አልፈራም፤ ሰው ምን ያደርገኛል?›› መዝ. ፶፮፥፫-፬ የሚለውን የመዝሙረኛውን ቃል አስብ፡፡ ሰዎች አንተን ምንም እንደማያደርጉህ እመን፤ ቀስ በቀስም ከሰዎች ጋር በመቀራረብ ማኅበራዊ ግንኙነትህን ልታሻሽል ትችላለህ፡፡

በአጠቃላይ ፍርሃት በራሱ መልካም ወይም ክፉ አይደለም፤ ማንን ነው የምንፈራው? ለምንድን ነው የምንፈራው? የሚሉት ጥያቄዎች ላይ ትኩረት መስጠት ይገባል፡፡ ከታሪክህ እንደተረዳነው ፍርሃትህ ተገቢ እንዳልሆነ ነው፡፡ አስቀድሞ ከዚህ ስሜት በቅጽበት ነጻ መውጣት እንደማይቻል ልትረዳ ያስፈልጋል፡፡ ነገር ግን በሂደት ተስፋ ሳትቆርጥ በእምነት ነጻ መውጣት ትችላለህ፡፡ ለዚህም በእግዚአብሔር ላይ ያለህ እምነት ሊያድግ እንደሚገባ ተረድተህ፤ ዘወትር በሃይማኖት ጸንተህ፤ በምክረ ካህን ተደግፈህ፤ እግዚአብሔርን ተስፋ እያደረግህ ልትጠባበቅ ይገባል፡፡

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር፤ ወወላዲቱ ድንግል፤ ወለመስቀሉ ክቡር*